
# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 11ኛ ክፍል



የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# ለመጽሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ




ይህን መጽሐፍ ብዙ ተማሪዎች ስለሚገለገሉበት በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባዋል፡፡

የሚከተሉት 10 ነጥቦች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዞ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ሃሳብ ይሰጣሉ፡፡

1. የመጽሐፉን ሽፋን በጠንካራ ወረቀት ወይንም በላስቲክ መሸፈን፡፡
2. መጽሐፉን ርጥበት በሌለበት ደረቅ ቦታ ላይ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፡፡
3. መጽሐፉን በቆሻሻ እጅ ያለማገላበጥና ገፆቹን ያለመግለጥ፡፡
4. በመጽሐፉ የሽፋንም ሆነ የውስጥ ገፆች ላይ አላስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችንና ጽሑፎችን ያለመሳልና ያለመጻፍ፡፡
5. ለመጽሐፉ የገጽ መለያ ወይንም የንባብ ማረፊያ የሆነ እልባት በጠንካራ ክርታስ ሠርቶ መጠቀም እንጂ የቆሙበትን ቦታ ለማስታወስ ገፆቹን ደጋግሞ ያለማጠፍ፡፡
6. ከመጽሐፉ ውስጥ አንድም ገጽ ሆነ ስዕል ገንጥሎ አለማውጣት፡፡
7. መጽሐፉ ቢገነጠል እንኳ በጥንቃቄ መልሶ በማጣበቂያ ማያያዝ፡፡
8. መጽሐፉ ቦርሳ ውስጥ ሲከተት እንዳይታጠፍና እንዳይጨማደድ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው በውሰት ሲሰጥ የተዋሰው ሰው በጥንቃቄ እንዲይዝ መንገር፡፡
10. መጽሐፉን በጥንቃቄ መግለጥ፣ ገፆቹ እንዳይገነጠሉና እንዳይወይቡ በጥንቃቄ መያዝ፡፡

# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

# 11ኛ ክፍል


አዘጋጅ፡- ፕሪን ኢንተርናሽናል አማካሪ ድርጅት

ጸሐፊ፡- አቶ ሰይፉ ይልማ

ቴክኒካል አማካሪዎች፡- ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ፣ አቶ አማረ አያሌው

አርታኢ፡- አቶ የሻው ተሰማ

ምልክት ቋንቋ፡- አቶ አማረ አያሌው

ግራፊክስ ዲዛይን፡- አቶ ፍቃደእግዚአብሄር ከበደ

የምልክት ቋንቋ ስዕል፡- አቶ ፍቃደእግዚአብሄር ከበደ

ሌሎች ስዕሎች፡- አቶ አሰፋ ጉታ

አስተባባሪዎች፡- ዶ/ር ጥላዬ ካሣሁን፣ ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ



የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

## ማውጫ

ምዕራፍ አንድ:

የአፍሪካ ኅብረት ---------------------------------------------------------------------------------- 2

ምዕራፍ ሁለት፡

ቃለ መጠይቅ ---------------------------------------------------------------------------------- 18

ምዕራፍ ሦስት፡

ባሕላዊ ሕክምና ---------------------------------------------------------------------------- 29

ምዕራፍ አራት፡

ትምህርት ---------------------------------------------------------------------------------------- 40

ምዕራፍ አምስት፡

ኢትዮጵያዊነት ---------------------------------------------------------------------------------- 50

ምዕራፍ ስድስት፡

የውኃ አጠቃቀም---------------------------------------------------------------------------------- 61

ምዕራፍ ሰባት፡

የምልክት ቋንቋ ሥነ ጽሑፍ -------------------------------------------------------------------- 77

ምዕራፍ ስምንት፡

ድህነት ---------------------------------------------------------------------------------------- 86

ምዕራፍ ዘጠኝ፡

ቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ --------------------------------------------------------------- 99

ምዕራፍ አስር፡

ኮምፒውተር ---------------------------------------------------------------------------------- 110

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ የተማሪው መጽሐፍ አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን ሐሳብን በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ የመቀበልና የመግለጽ ክሂሎትን ማዳበር ነው። ይህ የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ የተማሪው መጽሐፍ እነዚህን ዓላማዎች መሠረት በማድረግ የተመረጡ ይዘቶችን አካትቶ ቀርቧል።

ይህ መጽሐፉ አሥር ምዕራፎች አሉት። በእያንዳንዱ ምዕራፍ ምንባቦችን፣ ቃለ መጠይቆችን፣ አባባሎችን እንዲሁም በሦስቱ የምልክት ቋንቋ ክሂሎቶችና በምልክት ቋንቋ የእውቀት ዘርፎች ተለይተው የተሰናዱ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን ይዟል። በየምዕራፉ መጨረሻ የቡድን ውይይቶችን በማጠቃለያ መልክ ቀርበዋል። የቀረቡት የቡድን ውይይቶች ተማሪዎች የየምዕራፎችን ይዘት ምን ያህል እንደተረዱ የሚያመሳክሩባቸው ናቸው።

የመጽሐፉ ይዘት ለቅድመ ኮሌጅ ደረጃ እንዲመጥን ተገቢውን ጥንቃቄ ተደርጎለታል። በመሆኑም ተማሪዎችመጸሐፉን ሲጠቀሙ ግር እንዳይሰኙ ግልጽ መመሪያዎች፣ ልዩ ልዩ ማብራሪያዎችና አሥረጂዎች እንዲያካትት ተደርጓል። አቀራረቡም ተማሪዎች ግልጽ በሆነ መንገድ የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ክሂሎታቸውን እንዲያዳብሩ ለማገዝ በሚያስችል መልኩ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ መጽሐፉ ለኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ለመማር ዝንባሌ ላላቸው የመነሻ እውቀት ከማስጨበጡ ባሻገር፣ ለኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎች ደግሞ የመተርጎም እውቀታቸውን ለማሻሻል ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል።

በሌላ በኩል፣ ማንኛውም የመማሪያ መጽሐፍ ታትሞ በመማር-ማስተማሪያነት ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ፣ በተግባር እየተፈተሸና እየተገመገመ በየጊዜው የሚሻሻል ነው።


የአሥረኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና አልፋችሁ ለመሰናዶ ትምህርት መብቃታችሁ በጣም አስደሳች ነው:: ይህን እናንተ ያገኛችሁትን ዕድል ያላገኙ በርካታ ተማሪዎች አሉ:: በመሆኑም ከዚህ ይበልጥ ስኬታማ ትሆኑ ዘንድና በቀጣይ ለዩኒቨርሲቲ ቆይታችሁ ይረዳ ዘንድ ከፊታችሁ ያሉት ሁለት የመሰናዶ ዓመታት ወሳኝ ናቸው::

በመሆኑም ለስኬታማነታችሁ ይበልጥ ይረዳ ዘንድ ከእናንተና ከመምህሮቻችሁ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦችን መተግበር ይጠበቃል::

- መምህራችሁ መደበኛ የቤት ሥራዎችን ይሰጣችኋል::
- የተሰጣችሁን የቤት ሥራዎችን በሰዓቱ ሠርታችሁ ለመምህራችሁ ታቀርባላችሁ::
- ሁልጊዜ የምትማሯቸውን አዳዲስ ምልክቶች በደብተራችሁ ጽፋችሁ ትይዛላችሁ::
- የተማራችኋቸውን አዳዲስ ምልከቶችና የኢምቋ አገባቦችን በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ በመለማመድ የኢምቋ ክሂሎታችሁን ማዳበር ይኖርባችኋል::
- ከወቅታዊ ፈተናዎችና ሙከራዎች ባሻገር ድንገቴ ሙከራዎች ሊሰጣችሁ ስለሚችል ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን ይኖርባችኋል::
- እናንተም (ተማሪዎች)፣ መምህራችሁም በትምህርት ክፍለ ጊዜያት በሰዓቱ ክፍል ውስጥ መገኘት ይኖርባችኋል::
- መምህራችሁ፣ ተጋባዥ እንግዳና የተፈቀደለት ተማሪ ወዘተ በኢምቋ ገለጻ ሲያቀርብ፣ መልስ ሲመልስ፣ ጥያቄ ሲጠይቅ ወዘተ ሁላችሁም በጽሞና መከታተል ይኖርባችኋል::
- የትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ኢምቋ እንደመሆኑ፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ጥያቄ መጠየቅ፣ ገለጻ ማቅረብ፣ መልስ መመለስ፣ በቡድንና በጥንድ መወያየት የሚቻለው በኢምቋ ብቻ ነው::

# ምዕራፍ አንድ

## የአፍሪካ ኅብረት




ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፣

* የአፍሪካ ኅብረትን አመሠራረት በኢምቋ ትገልጻላችሁ፤
* አፍሪካ ኅብረትን ጠቃሜታ በኢምቋ ትወያያላችሁ፤
* በኅብረት መሥራት በተናጠል ከመሥራት ያለውን ጠቃሜታ በኢምቋ ትዘረዝራላችሁ፤
* የአፍሪካ ኅብረት ሀገራት ስሞችን በኢምቋና በጣት ፊደላት ታሳያላችሁ፤
* ከአፍሪካ ኅብረት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምልክቶች ትተነትናላችሁ፤
* የተለያዩ አቅጣጫዎችን በኢምቋ ታሳያላችሁ፤
* የኢምቋ ምልክቶችን እንደ አገባባቸው የመጠቀም ክሂሎቻችሁን ታዳብራላችሁ፡፡


## ቁልፍ ምልክቶች



አፍሪካ




ኅብረት




ሎጎ/አርማ




መሄድ




መምታት




ማለፍ




መታየት




መዳን




መድረስ




መውረድ




መፍታት



መቁረጥ



መጣል




መውሰድ




መፍጠር




መደብ




መራመድ




መዝጋት



መርከስ




ተራ




መቀባት




መቻል



አጭር




መጥለፍ




መስፈር




ቀውስ




ማደር/ማደሪያ




መውለድ



መቀመጥ



መቀበል



ሐሳብን መቀበል

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## የአፍሪካ ካርታ መመልከትና መግለጽ

ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረበውን የአፍሪካ ካርታ ተመልክታችሁ ከካርታው በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በኢምቋ መልሱ።




ከላይ የቀረበውን የአፍሪካ ካርታ በጥንቃቄ ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን በኢምቋ ለመምህራችሁ ግለጹ?

1. ሰዎች ወይም ሀገራት የሚተባበሩት ለምንድን ነው?
2. አንድ ነገር በኅብረት ነው የተሠራው ማለት ምን ማለት ነው?
3. በካርታው ላይበቅኝ ግዛት ያልተያዘች ሀገር ለይታችሁ በኢምቋ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

### ዕይታዊ ንባብን ማዳበር

ከዚህ በላይ የቀረበውን የአፍሪካ ካርታ በጥንቃቄ ተመልክታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት በኢምቋ መልሱ።

1. ግብጽ የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገር ናት።
2. በካርታው ላይ እንደምትመለከቱት፣ በውኃ ከተከበቡ ሀገራት መካከል አንዱ ማዳጋስካር ነው።
3. በካርታው ላይ እንደምትመለከቱት፣ ሰፊየቆዳ ስፋት ያለው ሀገር አልጀሪያ ነው?
4. በካርታው ላይ እንደምትመለከቱት፣ ኬንያ ከኢትዮጵያ በስተሰሜን ትገኛለች።

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### አንብቦ መረዳት

የአፍሪካ ኅብረት የሚለውን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ፣ የምንባቡን ፍሬ ሐሳብ ለመምህራችሁ በኢምቋ ግለጹ።

#### የአፍሪካ ኅብረት

አፍሪካ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚነገሩበት 29, 922, 059 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ያለውና 1, 186, 035, 272 ሕዝቦች የሚኖሩበት ግዙፍ አህጉር ነው። የአፍሪካ ኅብረት እኤአ ግንቦት 25 ቀን 1963 በአዲስ አበባ ተመሥርቶ የድርጅቱ መመሪያ ውል (ቻርተር) በሠላሳ ሁለት መሥራች የሀገራትመሪዎች ተፈርሟል። አፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሠረተ ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች ነበሩት። የመጀመሪያው የአህጉሩን አንድነትና ትብብር ለማራመድና ደርጅቱ የአፍሪካውያን የጋራ ልሣን እንዲሆን ሲሆን፣ ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ በዚያን ጊዜ ከቅኝ ግዛት ቀንበር ነጻ ያልወጡ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ስለነበሩ፣ የእነሱን ነጻነት ዐቢይ ዓላማ አድርጎ መታገል ነበር። በሌላ በኩል፣ አባል ሀገራት እንደ ቀድሞው በቅኝ ግዛት ቁጥጥር ሥር እንዳይውሉ ለማስቻል ነበር።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሠረት የድርጅቱም ጠቅላይ መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ እንዲሆን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት፣ የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ይገኛል።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከምሥረታው ጀምሮ ይጠራበት የነበረውን "አፍሪካ አንድነት ድርጅት" የሚለውን ስያሜ ወደ " አፍሪካ ኅብረት" የተቀየረው እኤአ ሐምሌ 2 ቀን 1994 በአዲስ አበባ ከተማ በተወሰነው ውሳኔ ነው። የአፍሪካ ኅብረት በሠላሳ ሁለት መሥራች መሪዎች የተመሠረተ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት ሁሉም የአፍሪካ ሀገራት የኅብረቱ አባላት ናቸው።

የአፍሪካ ኅብረት፣ በጋራ መበልጸግ፣ ቅኝ ግዛትን በጋራ መከላከል፣ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊናፖለቲካዊመስተጋብሮችን ማጠናከር፣ በሀገራት መካከል የሚፈጠሩ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት፣ በሀገራት ውስጥ የሚከሰቱ የእርስ በርስ ግጭቶችን መፍታት፣ ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን በጋራ መከላከል፣ ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን ማዳበርና ማሳደግ፣ የአፍሪካ ሕዝቦችን የኑሮ ደረጃ ማጎልበት በሚሉና ሌሎችን ተዛማጅ ጉዳዮችን በመተግበር ላይ የሚገኝ ኅብረት ነው::

በመዋቅር ደረጃ፣ የአፍሪካ ኅብረት የአስተዳድርና የፖለቲካ ጉዳዮች በሚባሉ ሁለት ክፍሎች የተዋቀረ ነው:: አፍሪካ ኅብረት ታላላቅ ውሳኔዎች የሚወሰኑት የኅብረቱ ሀገራት ሕጋዊ ተወካዮች ወይም መንግሥታት በተገኙበት በኅብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ነው::

የየአፍሪካ ኅብረት ለአፍሪካ ሀገራት የጋራ ጉዳይ የሚሠራ በመሆኑ፣ ጉባኤውን የሚመራ ፕሬዚዳንት (የጉባኤው መሪ) አለው::

የአፍሪካ ኅብረት የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በጋራ ያቋቋሙት ድርጅት እንደመሆኑና፣ የኅብረቱ አባል ሀገራትም የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ በመሆናቸው፣ እንደ ቋንቋዎቹ ልዩነት ኅብረቱም በተለያዩ ሀገራት የተለያዩ ስያሜዎች አሉት:: ለምሳሌ፣በአማርኛ “አፍሪካ ኅብረት”፣ በእንግሊዝኛ አፍሪካን ዩኒየን (AFRICAN UNION)፣ በፈረንሳይኛ ዩኒየን አፍሪካኔ (UNION AFRICANE)፣ በፖርቹጋል ዩኒዮ አፍሪካና (UNIAO AFRICANA)፣ በስፓኝ ዩኒዮን አፍሪካና (UNION AFRICANA)፣ በኪስዋሕሊ ኡሞጃ ዋ አፍሪቃ (UMOJA WA AFRIKA)፣ በኢምቋ ደግሞ ከላይ በሥዕሉ እንደሚታው “አፍሪካ” ና “ኅብረት” የሚሉ ሁለት ምልክቶችን በማጣመር ይገለጻል::

*(ምንጭ፣ ከአፍሪካ ኅብረት ድረገጽ ለዚህ ጽሑፍ እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ::)*



## መልመጃ አንድ

በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ በጽሑፍ ከመለሳችሁ በኋላ ለመምህራቸሁ በኢምቋ አሳዩ::

1. የአፍሪካ ኅብረት ስንት አባል ሀገራት አሉት?
2. የአፍሪካ ኅብረት የተመሠረተበት ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶችን ምን-ምን ናቸው?
3. የአፍሪካ ኅብረት ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል አራቱን ዘርዝሩ::
4. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት የአፍሪካ ኅብረት መጠሪያዎች ምን-ምን ናቸው?
5. የአፍሪካ ኅብረት በተለያዩ መጠሪያዎች የሚጠራበት ምክንያት ምንድን ነው?
6. የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ በአዲስ አበባ እንዲሆን የኅብረቱን ሀገራት መሪዎች ያሳመኑ መሪ ማን ይባላሉ?
7. የአፍሪካ አህጉር ጠቅላላ ስፋት ምን ያህል ነው?
8. በምንባቡ መሠረት በአፍሪካ ምን ያህል ሕዝቦች ይኖራሉ?
9. የአፍሪካ ኅብረት ለመመሥረት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያበረከቱ ሁለት ሀገራት ስም ለመምህራችሁ በኢምቋ አሳዩ::



# ክፍለ ትምህርት አራት

ከዚህ በታች የቀረበውን የምልክቶች አገባባዊ አገላለጽ ከመምህራችሁ ጋር በጋራ እያነበባችሁ ተለማመዱ።

## የምልክቶች አገባባዊ አገላለጽ

የምልክቶች አገባባዊ አገላለጽ የሚባለው አንድ ምልክት በተለያዩ አገባቦች የተለያዩ ምልክቶች ሲኖሩት ነው። የምልክት ቋንቋ አገባባዊ አገላለጽ የተግባቦት ፋይዳውን ይበልጥ ግልጽ ከማድረጉም ባሻገር በብዙዎች ዘንድ " ምልክት ቋንቋ የተሟላ ቋንቋ አይደለም " ፤ " ሐሳብን ለመግለጽ የምልክቶች እጥረት አለ " ፤ " የተሟላ ምልክት ስለሌለ ምልክት ቋንቋ ለማስተማርም ሆነ ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው " እነዚህንና መሰል በምልክት ቋንቋ ዙሪያ የሚሰነዘሩ የተሳሳቱ መላምቶች አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት ከፍተኛ ሚና አለው።

በመሆኑም አንዳንድ የአማርኛ ቃላት (ብዙውን ጊዜ ግሶች) እንደ አገባባቸው የተለያዩ ምልክቶች አሏቸው። እነዚህን አገባባዊ ምልክቶች መረዳት በምልክት ቋንቋ በሚገባ ለመግባባት የግድ ከመሆናቸው ባሻገር፣ለቋንቋው ተርጓሚዎችና አስተማሪዎች ከፍተኛ ሚና አለው።

ከላይ የቀረበውን ሐሳብ ይበልጥ ግልጽ ያደርግልን ዘንድ የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንመልከት።

### መሄድ

ውኃ ሄደ (ውኃና የለም ወይም ባዶ በሚሉ ሁለት ምልክት ይገለጻል)

መብራት ሄደ (መብራትና ጠፋ በሚሉ ሁለት ምልክት ይገለጻል)

ወደ ክፍለ ሀገር ሄደ (ክፍለ ሀገርና መሳፈር በሚሉት ሁለት ምልክቶች ይገለጻል)

በታክሲ መሄድ (የታክሲ ምልክትን ሠርቶ ከግራ ወደ ቀኝ መውሰድ)

ውጪ ሀገር መሄድ (የአውሮፕላን ምልክት ሰርቶ ወደ ቀኝ ከፍ ማድረግ)

### መምታት

ከበሮ መምታት

አድማ መምታት

ኳስ መምታት

በዱላ መምታት

በጥፊ መምታት

### መምጣት

መብራት መጣ (በራ በሚለው ምልክት ይገለጻል)

ውኃ መጣ (ውኃ አለ በሚለው ምልክት ይገለጻል)

ከክፍለ ሀገር መጣ (መሳፈር የሚለው ምልክት ከውጪ ወደ ውስጥ በማንቀሳቀስ ይገለጻል።)

በታክሲ መጣ (ታክሲ የሚለውን ምልክት ሠርቶ ከውጪ ወደ ውስጥ በማንቀሳቀስ ይገለጻል።)

## ማለፍ

ችግርን ማለፍ (ይህ ምልክት እንደ አገባቡ በሁለት የተለያዩ ምልክቶች ሊገለጽ ይችላል። ችግርን በትዕግስት ማለፍና ችግርን ተቋቁሞ ማለፍ)

ፈተና ማለፍ (ፈተናና ማለፍ በሚሉ ዘወትራዊ ምልክቶች ይገለጻል።)

ጥሎ ማለፍ (ለተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች የሚገለጽ ስለሆነ፣ መወዳደርና ማሸነፍ በሚሉት ሁለት ምልክቶች ይገለጻል።)

የተከለከለ ወይም የተከለለ ቦታን ማለፍ (እንደ የተከለከለው ቦታ በተለያዩ ምክቶች ይገለጻል።)

የትራፊክ ሕግ መተላለፍ (ትራፊክ፣ ሕግና መስበር በሚሉት ሦስት ምልክቶች ይገለጻል።)

ዓይቶ ማለፍ (ዓይተን እንዳላየ ሆነን ማለፋችንን ለመግለጽ።)

የቴሌቪዥን ወይም የሬድዮ ፕሮግራም መተላለፍ ( ቴሌቪዥን/ሬድዮና ስርጭት በሚሉት ሁለት ምልክቶች ይገለጻል።)

የበሽታ መተላለፍ (በሽታና መተላለፍ በሚሉት ሁለት ምልክቶች ይገለጻል።)

ሳናየው ያለፈንን ነገር ለመግለጽ (ለምሳሌ ቴሌቪዥን ወይም የሬድዮ ፕሮግራም ሲያልፈን፣ አንድ ሰው ወይም ሌላ ነገር ሳናየው በአጠገባችን ሲያልፍ) (አመለጠኝ በሚለው ምልክት ይገለጻል።)

መተላለፍ (ኃጥአት መሥራታችንን ለመግለጽ) (ኃጥአት በሚለው ምልክት ይገለጻል።)

አለፈልኝ (ኑሮዬ ተሻሻለ በሚለው ምልክት ይገለጻል)

## መቁላት

ቡና ወይም ጥራጥሬ መቁላት (የቀኙን አመልካች ጣት ቆልምሞ በግራ መዳፍ ላይ ወደፊትና ወደ ኋላ ማመላለስ)

የውሻ ጭራ መቁላት (ውሻው ጌታውን ሲያይ ጭራውን ይቆላል።)

ቁሌታም (የዚህን ምልክት ሐሳብ ለተማሪዎች ይግለጹላቸውና እነሱ ምልክቱን እንዲያሳዩ ያድርጉ።)

## መታየት

በቴሌቪዥን፣ በዜና፣ በተውኔት ፣ ወዘተ፣ መታየት (ትላንት በቴሌቪዥን ታየሁ ለማለት፣)

በዐይነቁራኛ መታየት (ማነፍነፍ በሚለው ምልክት ይገለጻል::)

በትኩረት መታየት (በትኩረት መታየት ያለበት ጉዳይ ነው ለማለት፣)

በኮሚቴ መታየት (ኮሚቴና መወያየት በሚሉ ሁለት ምልክቶች ይገለጻል::)

እንደ ሕጻን መታየት (አሻንጉሊት የሚለውን ምልክት በፊት እንቅስቃሴ የንቀት ሁኔታን ከማሳየት ጋር በማጣመር ይገለጻል::)

በሐኪም መታየት (መመርመር በሚለው ምልክት ይገለጻል::)

በህልም መታየት (ህልምና በህልም የታየው ነገርን በሚገልጹ ሁለት ምልክቶች ይገለጻል::)

በንቀት፣ በጥላቻ፣ በፍቅር፣ ወዘተ  መታየት (እንደ ሁኔታው በተለያዩ ምልክቶች ይገለጻል)

አሸብርቆ መታየት (አምሮ መታየት)

## መዳን

ከአደጋ መዳን (አደጋና ማምለጥ በሚሉ ሁለት ምልክቶች ይገለጻል::)

ከበሽታ መዳን (ፈውስ በሚለው ምልክትይገለጻል::)

ከኃጥአት መዳን (ኃጥአትና ይቅርታ በሚሉት ሁለት ምልክቶች ይገለጻል::)

## መድረስ

አንድ የተወሰነ ቦታ መድረስ

በዓል ደረሰ (ቀኑ ተቃረበ ለማለት፣)

መጽሐፍ ደረሰ (ጻፈ ለማለት፣)

ሎተሪ ደረሰኝ (ዕድለኛ ሆነኩ ወይም አሸነፍኩ ለማለት፣)

## መውረድ

ከስልጣን መውረድ

ደረጃ መውረድ

ዝናብ ወረደ

ወጡ ከማንደጃው ወረደ

ከመሰላል መውረድ

የችሎታ መውረድ (መድከም ወይም የችሎታ መቀነስ)

ከሰማይ መውረድ (እንደ የጌታ ከሰማይ መውረድ፣ መና ከሰማይ መውረድ ፣ ቁርዐን ከሰማይ መውረድ የመሳሰሉትን ለመግለጽ፣)

እስክስታ መውረድ

### መፍታት

ከእስር መፈታት (ከወኅኒ መውጣትን ለመግለጽ፣)

ከእስር መፈታት (ለእንስሳ፣ በተለይ ለውሻ፣)

እግዚአብሔር ይፍታህ (ይማርህ ለማለት፣)

ጾም መፍታት (ጾምና መጨረስ በሚሉ ሁለት ምልክቶች ይገለጻል።)

### መብላት

ምግብ መብላት

ቁማር መብላት

በአውሬ መበላት

በንግድና በገበያ ቦታዎች ብር መበላት፣ (በ ጠብቆ ይነበባል ፤ ተሸወድኩ ወይም ተታለልኩ ለማለት፣)

### መውጣት

ተራራ መውጣት

ከቤት መውጣት

መሰላል መውጣት

### መቁረጥ

ጨርቅ መቁረጥ

ተስፋ መቁረጥ

እንጨት መቁረጥ

ዳቦ ቆሎ መቁረጥ

ሥጋ መቁረጥ

አንድ ነገር ለማድረግ መቁረጥ (መወሰን)

### መጣል

እንቁላል መጣል (እንቅላልና መውለድ በሚሉት ሁለት ምልክቶች የሚገለጽ ሲሆን እንቁላል መፈልፈል የሚለውን ለመግለጽ ደግሞ መውለድ የሚለውን ምልክት መደጋገም ያስፈልጋል።)

ዕቁብ መጣል (ዕቁብና መክፈል በሚሉት ሁለት ምልክቶች ይገለጻል።)

ጠጅ መጣል (ጠጅና ማዘጋጀት በሚሉት ሁለት ምልክቶች ይገለጻል።)

በጠረባ መጣል

እቃ መጣል (መጥፋቱን ለመግለጽ፣)

እቃ መጣል (ከእጅ አምልጦ መውደቁን ለመግለጽ፣)

ዕጣ መጣል

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በላይ በቀረቡት የኢምቋ አገባባዊ አገላለጾች ካነበባችሁ በኋላ፣ለሚከተሉት ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላት አገባባዊ ምልክቶች ሥሩላቸው።

1. መጥፋት
2. መውሰድ
3. መፍጠር
4. መዘጋት
5. ተራ
6. መቀመጫ/መቀመጥ/
7. አጭር
8. መጥለፍ

## መልመጃ ሦስት

ከዚህ በታች በተለያየ አገባብ ለቀረቡት ምልክቶች እንደ አገባባቸው የሚወክሏቸውን ምልክቶች ለመምህራችሁ አሳዩ።

*ሀ. ማደር/ ማደሪያ/ እዳሪ*

1. ጓደኛዬ ደኅና እደሩ ብሎ ተሰናብቶ ወጣ።
2. የጓደኛዬ እህት እርኩስ መንፈስ ስላደረባት ሁል ጊዜ ማታ ማታ ትጮኻለች።

3. በየመንገዱ የሚታየው *እጻሪ* ከተማዋን መልካም ገጽታ አበላሽቶታል፡፡

4. አዛውንቱ "*ሳይውል ሳያድር* የበደላችኋቸውን ሰዎች ይቅር በሏቸው" ብለው መከሩን፡፡

*ለ. መሰፈር*

1. እኛ *ሰፈር* ብዙ ውሾች አሉ፡፡
2. ወታደሮቹ የተሰጣቸውን የሸራ ድንኳን እየተከሉ ሜዳው ላይ *መሰፈር* ጀመሩ፡፡
3. ሽምሱ ለእናቴ ሁለት *መስፈሪያ* ጨው በአንድ ብር ሸጠላት፡፡
4. *በሰፈሩት* ቁና ይሰፈራልና፣ በሰው ላይ ተንኮል አትሥሩ፡፡

*ሐ. መውለድ*

1. የክፍሎም ሚስት መንታ *ወለደች፡፡*
2. የእስልምና እምነት ተከታዮች የባንክ *ወለድ* አይቀበሉም፡፡
3. ውኃ *ወለድና* አየር *ወለድ* በሽታዎችን ለመከላከል ሁሉም ሰው አካባቢውን ማጽዳት አለበት፡፡

*መ. ቀሪ*

1. መምህሩ ለአልማዝ ብዙ ቀን ከክፍል ስለ*ቀረች* ፈተና አትፈተኚም አሏት፡፡
2. እኔና ጓደኛዬ ሆቴል ገብተን ምሳ የበላንበትን ሒሳብ ከፍለን *ቀሪውን* ለአስተናጋጇ ጉርሻ ሰጥተን ወጣን፡፡
3. ይህን *ኋላቀር* አስተራረስ ካላሻሻልን የምግብ እጥረት ሊያጋጥመን ይችላል፡፡

*ሠ. መቀመጥ*

1. መምህሩ ክፍል ሲገቡ ቆመው የተቀበሏቸውን ተማሪዎች አመስግነው "*ተቀመጡ*" አሏቸው፡፡
2. የአፍሪካ ኅብረት *መቀመጫ* አዲስ አበባ ነው፡፡
3. የርእሰ መምህራችን የቢሮ *መቀመጫ* በጣም ዘመናዊና ምቹ ነው፡፡
4. የአዚዛ ልጅ ለበዓል የበላው ምግብ ስላልተስማማው በተደጋጋሚ *አስቀመጠው፡፡*
5. ገንዘብ *ማስቀመጥ* ብዙ ጠቃሜታዎች አሉት፡፡

*ረ. መጠየቅ*

1. የታመመ፣ ጉዳት የደረሰበት፣ የተቸገረ፣ ሰው *መጠየቅ* የሥነ ምግባር መገለጫ ነው፡፡
2. ጥያቄ *መጠየቅ* የማናውቀውን እንድናውቅ ያደርጋል፡፡
3. ብዙ ጊዜ *ቃለ መጠይቅ* የሚደረግላቸው ታዋቂ ሰዎች ናቸው፡፡

*ሰ. መቀበል*

1. ከእናቶቻችንና ከአባቶቻችን *የተቀበልነውን* ገንዘብ በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል።
2. የእናቶቻችንን ምክር *መቀበል* ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት።

*ሸ. ረዥም*


1. ሰውየው በጣም *ረዥም* ነው።
2. ገመዱ በጣም *ረዥም* ስለሆነ በቀላሉ ለማሰር ይመቻል።

*ቀ. ቀውስ*

1. አብዝቶ መጨነቅ የአእምሮ *መቃወስ* ሊያስከትል ይችላል።
2. የነዳጅ ዋጋ አላግባብ መጨመር የኢኮኖሚ *ቀውስ* ያስከትላል።
3. ሰላም *የሚያቃውሱ* ብዙ ነገሮች አሉ

## የኢምቋ ምልክቶች ትንተና

ምሳሌ አንድ *አፍሪካ*



| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ:- | ገ እና የጉርሻ ቅርጽ |
| የመዳፍ አቅጣጫ:- | ወደ ውጭ |
| የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ:- | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ:- | የ ገ እጅን አሽከርክሮ ወደታች በማውረድ የጉርሻ ምልክት መሥራት |
| የፊት/የሰውነት እንቅስቃሴ:- | የለውም |
| ምልክቱ የሚሠራበት እጅ:- | በአንድ እጅ |



ምሳሌ ሁለት ኅብረት

| | |
|---|---|
| የእጅ ቅርጽ፡- | በሁለቱም እጆች “ ሐ ” |
| የመዳፍ አቅጣጫ፡- | ወደ ውጪ |
| የእጅ የሚያርፍበት ቦታ፡- | ከደረት ትይዩ |
| የእጅ እንቅስቃሴ፡- | የሁለቱንም “ ሠ ” እጆች በአውራ ጣትና አመልካች ጣት አቆላልፎ ማሽከርከር |
| የፊት/የሰውነት እንቅስቃሴ፡- | የለውም |
| ምልክቱ የሚሠራበት እጅ | በሁለት እጅ |

## መልመጃ አራት

ከዚህ በላይ የቀረቡትን የምልክቶች ትንተና ምሳሌ መሠረት በማድረግ፣ የሚከተሉትን ምልክቶች ተንትኑ።

1. አህጉር
2. ማኅልበት
3. ፖለቲካ
4. ባርነት
5. ነጻነት

# ክፍለ ትምህርት አምስት


## የቡድን ውይይት

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፤ በቡድን ሆናችሁ፣ ከዚህ በታች በተሰጡት ጥያቄዎች ዙሪያ ተወያዩ፤ የውይይታችሁንም ፍሬ ሐሳብ በተወካዮቻችሁ አማካይነት በኢምቋ ለክፍሉ ተማሪዎች አቅርቡ።

1. በኅብረት መሥራት ምን-ምን ጠቃሜታዎች አሉት?
2. አፍሪካን ከበለጸጉ ሀገራት እኩል ለማድረግ ከሀገር መሪዎች፣ ከተማሪዎች፣ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከመምህራንና ከምሁራን ምን ይጠበቃል?
3. ምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሱት የቅኝ ግዛት ተጽዕኖዎች በተጨማሪ፣ ሌሎች የምታውቋቸው የቅኝ ግዛት ችግሮችን ዘርዝሩ።

# ምዕራፍ ሁለት

## ቃል መጠይቅ




ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፣

* የቃለ መጠይቅ ትርጉምና ጽንሰ ሐሳብ በኢምቋ ትገልጻላችሁ፤
* ቃለ መጠይቅ የሚደረግባቸው ዓላማዎችን በኢምቋ ትዘረዝራላችሁ፤
* ቃለ መጠይቅ የማዘጋጀት ክሂላችሁንታዳብራላችሁ፤
* ለቃለ መጠይቅ ዝግጁ ትሆናላችሁ፤
* መስማት ከተሳናቸው ግለሰቦች ጋር ቃለ መጠይቅ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችንና ሁኔታዎችን ትለያላችሁ፤
* የኢምቋ ሰዋስው አጠቃቀም ክሂላችሁን ታዳብራላችሁ::


## ቁልፍ ምልክቶች




ቃለ መጠይቅ



ጥያቄ መጠየቅ



ድምጽ ማጉያ



ምን




ለማን




ለምን



እንዴት




የት




የትኛው




መቼ



በመጨረሻ



በመጀመሪያ




መግባባት



ንግግር



በቅድሚያ /በመጀመሪያ



ሃሳብ

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መመልከትና መግለጽ



ከዚህ በላይ የቀረበውን ሥዕል መሠረት በማድረግ፣የሚከተሉትን ጥያቄዎች በኢምቋ መልሱ።

1. በወጣቱ ዙሪያ ያሉት ሰዎች ተግባራችው ምንድን ነው?
2. እነዚህ ሰዎች ወጣቱን ለምን የከበቡት ይመስላችኋል?
3. ወጣቱ ስለ ምን እየተናገረ ያለ ይመስላችኋል?
4. ወጣቱ ቃለ መጠይቅ ማድረጉ ምን-ምን ጠቃሚታዎች አሉት?

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

### አንብቦ መረዳት

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በአንቀጽ በአንቀጽ ተከፋፍላችሁ ካነበባችሁ በኋላ፣ የእያንዳንዱ አንቀጽ ፍሬ ሐሳብ ለክፍል ተማሪዎች በኢምቋ አቅርቡ።

## የቃለ መጠይቅ ምንነትና ዓላማዎች

እያንዳንዱ ሰው በዕለት ተዕለት ሕይወቱ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ይገናኛል፤ በግንኙነቱም የተለያዩ ንግግሮችን ያደርጋል:: በንግግሩም ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ይሰጣል:: በአንጻሩም ጥያቄዎችን ይጠይቃል:: ይህ የተግባቦት ሒደት ቃለ መጠይቅ ተብሎ ይጠራል:: ቃለ መጠይቅ የቃል ጥያቄ አዳምጦ ለተጠየቀውም ጥያቄ የቃል መልስ መስጠት ተብሎ በአጭሩ ሊገለጽ ይችላል:: አብዛኛውን ጊዜ ቃለ መጠይቅ የሚደረገው በሁለት ሰዎች መካከል ሲሆን፣ አንደኛው ጠያቂ ሁለተኛው ተጠያቂ ይሆናሉ::

ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ አንድ ተጠያቂ ለብዙ ጠያቂዎች መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል:: አንድ ተጠያቂ ለብዙ ጠያቂዎች መልስ ሊሰጥባቸው ከሚችልባቸው ሁኔታዎች መካከል፣ አንድ የሀገር መሪ ወይም ባለሥልጣን ለብዙ ጋዜጠኞች መልስ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች፣ አንድ ታዋቂ ሰው (አርቲስት፣ ስፖርተኛ፣ ወታደር፣ ተመራማሪ፣ ወዘተ፣) ለብዙ ጠያቂዎች መልስ የሚሰጥባቸው አጋጣሚዎች ይጠቀሳሉ:: ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች ጭውውት በሚያደርጉበት ጊዜም አንድ ሰው ለብዙ ጠያቂዎች መልስ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ::

በርካታ የቃለ መጠይቅ ዓይነቶች አሉ:: በዋናነት በስልክ የሚደረግ ቃለ መጠይቅ፣ ፊት ለፊት የሚደረግ ቃለ መጠይቅ፣ የፓናል ውይይት/ቃለ መጠይቅ/፣ የቡድን ውይይት (በቡድን የሚደረግ ቃለ መጠይቅ)፣ ብዙ ሰዎች በአንድ ላይ ሆነው ተራ በተራ ቃለ መጠይቅ የሚደረጉበት ቃለ መጠይቅ፣ በምሳ ወይም በእራት ግብዣ ላይ የሚደረግ ቃለ መጠይቅ፣ ለብቃት ማረጋገጫ የሚደረግ ቃለ መጠይቅና መደበኛ ቃለ መጠይቅ ተብለው ሊዘረዘሩ ይችላሉ::

ለተለያዩ ዓላማዎች የተለያሉ ቃለ መጠይቆች ይዘጋጃሉ:: ከነዚህም መካከል በዋናኛነት የሚጠቀሰው ሥራ ለመቀጠር የሚደረግ ቃለ መጠይቅ ነው:: ሥራ ለመቀጠር የሚደረግ ቃለ መጠይቅ የሚባለው፣ አንድ ሰው መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት ውስጥ ሥራ ለመቀጠር ሲጠራ ቀጣሪው አካል አመልካቹን ከመቅጠሩ በፊት ለሥራው ብቁ መሆን/አለመሆኑን በተለያዩ መመዘኛዎች ያረጋግጣል:: ከነዚህም የብቃት ማረጋገጫዎች አንዱ ቃለ መጠይቅ ነው:: አመልካቹ የሚደረግለት ቃለ መጠይቅ ድርጅቱ ዓላማና አሠራር ሊለያይ ይችላል::

ከዚህ በላይ ከተገለጹት በተጨማሪ፣ቃለ መጠይቅ ጥናታዊ ጽሑፍ ለመሥራት ሲፈለግም በጥቅም ላይ ይውላል:: የተለያዩ ተመራማሪዎች ቃለ መጠይቅን እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ ይጠቀሙበታል:: በሌላ በኩል በተለያየ ጉዳይ ላይ መረጃ ማግኘት የሚፈልጉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ቃለ መጠይቅ ያደርጋሉ:: ቃለ መጠይቅ የሚያደርገው ድርጅት በጎ አድራጎት ድርጅት ከሆነ የማኅበረሰቡን ችግሮች ለመፍታት ከማኅበረሰቡ መረጃ ለማግኘት ቃለ መጠይቅ ሊያደርግ ይችላል:: ቃለ መጠይቅ የሚያደርገው ድርጅት አትራፊ ድርጅት ከሆነ ደግሞ፣በአንድ የተወሰነ አካባቢ ወይም በአንድ አካባቢ ምን ዓይነት ንግድ እንደሚያዋጣ በቃለ መጠይቅ መረጃ ሊያሰባስብ ይችላል::

አብዛኛውን ጊዜ ቃለ መጠይቅ የሚደረገው በቃል ቢሆንም፤ የሚደረገውን ቃለ መጠይቅ በመቅረጸ ድምጽ በመቅዳት ለሌሎች እንዲተላለፍ ይደረጋል:: ይኸውም አንድ የሀገር መሪ ለጋዜጠኞች መግለጫ በሚሰጥበት ጊዜ የሚሰጠው መግለጫ ለሕዝቡ እንዲዳረስ መግለጫውን በምስልና በድምጽ በመቅዳት ይሠራጫል:: መቅረጸ ድምጽ በሌለበት አጋጣሚ የሚደረገውን ቃለ መጠይቅ በጽሑፍ በማስቀረት መረጃው ሳይዛነፍ ቃል በቃል መያዝ ይቻላል::

በመሆኑም አንዳንድ ጊዜ መቅረጸ ድምጽና የጽሕፈት መሣሪያዎች ለቃለ መጠይቅ አስፈላጊ ግብዓቶች ናቸው:: የሚደረገው ቃለ መጠይቅ በመገናኛ ብዙኃን ለሕዝብ እንዲተላለፍ ከተፈለገ ወይም የሚደረገው ቃለ መጠይቅ በመድረክ ቀርቦ ለተሰብሳቢዎች የማይሰማ ከሆነ፣ ሁሉም ተሰብሳቢዎችና የመገናኛ ብዙኃን ተከታታዮች የጠያቂውና መልስ ሰጪው ድምጽ ጎላ ብሎ እንዲሰማ የድምጽ ማጉያ መሣሪያ በእጅጉ አስፈላጊ ነው::

በአጠቃላይ ቃለ መጠይቅ የሁሉም ሰው የዕለት ተዕለት የሕይወት ክስተት ነው:: ቃለ መጠይቅ ሰላምታ ከመለዋወጥ ጀምሮ እስከ ታላላቅ የንግድ፣ የትምህርት፣ የምርምርና ሌሎችም ለሰው ልጆች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ለማሟላት አስፈላጊ የሆነ የተግባቦት ሒደት ነው::

## መልመጃ አንድ

ከላይ የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በኢምቁ መልሱ::

1. ሰዎች ለምን ቃለ መጠይቅ ያደርጋሉ?
2. የቃለ መጠይቅ ዓይነቶችን ዘርዝሩና፣ የእያንዳንዳቸውን መሠረተ ሐሳብ አብራሩ::
3. ዕጩ ተመራቂ ተማሪዎች ቃለ መጠይቅ የሚያደርጉት ለምንድን ነው?
4. ድርጅቶች ቃለ መጠይቅ የሚያደርጉበት ምክንቶች ምን-ምን ናቸው?
5. ለሥራ ቅጥር የሚደረግ ቃለ መጠይቅ ምን-ምን ጠቃሚታዎች አሉት?
6. “ቃለ መጠይቅ”፣ “ጥያቄ መጠየቅ”፣ “የታመመ ሰው መጠየቅ” እነዚህ ሦስት ምልክቶችን የሚወክሉ ሐረጋት በኢምቁ እንዴት እንደሚገለጹ ለመምህራችሁ አሳዩ::

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### የኢምቋ ሰዋስው ምልከታ

1. ቃለ መጠይቅ ማለት ምን? (ቃለ መጠይቅ ማለት ምን ማለት ነው?)
2. እናንተ ማወቅ ቃለ መጠይቅ ዓይነት ስም ጻፉ::(የምታውቋቸውን የቃለ መጠይቅ ዓይነቶችን ግለጹ)
3. ቃለ መጠይቅ ጥቅም ምን?(የቃለ መጠይቅ ጥቅም ምንድን ነው?)
4. ቃለ መጠይቅ ጥቅም ስም ስም ጻፍ:: ( ከቃለ መጠይቅ የሚገኙ ጠቃሜታዎችን ዘርዝሩ)
5. ቃለ መጠይቅ ዓላማ ምን? (ቃለ መጠይቅ የሚደረግባቸው ምክንያቶች ምን-ምን ናቸው ?
6. ቃለ መጠይቅ በፊት አስፈላጊ ዝግጅት ምን ? (በቃለ መጠይቅ ለማድረግ የሚያስፈልጉ

ዝግጅቶች ምን-ምን ናቸው?)

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በላይ የቀረበውን የኢምቋ ሰዋስው ምሳሌ ተመልክታችሁ፣የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. ከዚህ ቀደም ቃለ መጠይቅ አድርጋችሁ ታውቃላችሁ?
2. በጎ አድራጎት ደርጅቶች ቃለ መጠይቅ የሚያደርጉት ለምንድን ነው?
3. ከናንተ መካከል ቃለ መጠይቅ አድርጎ የሚያውቅ ሰው አለ?
4. ለቃለ መጠይቅ የሚያስፈልጉ ግብአቶች ምን-ምን ናቸው?
5. አብዛኛውን ጊዜ ቃለ መጠይቅ የሚደረገው በስንት ሰዎች ነው?



# ክፍለ ትምህርት አራት

መስማት ከተሳናቸው ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን መለየት፡፡

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በማንበብ፣ የምንባቦችን ፍሬ ሐሳብ ከመግለጽ በተጨማሪ ሌሎች መካተት ያለባቸውን ሐሳቦች በኢምቋ ግለጹ፡፡

መስማት የተሳነው ግለሰብ ስንል የድምጽ ንግግር በጆሮ መስማት የማይችል ማለት ነው፡፡ በጆሮው ድምጽ አይሰማም ማለት ግን ሌላ መግባቢያ የለውም ወይም መግባባት አይችልም ማለት አይደለም፡፡ መስማት የተሳናቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የራሳቸው መግባቢያ ቋንቋ አላቸው፡፡

መስማት የተሳናቸው የሚግባቡበት ቋንቋ የምልክት ቋንቋ ይባላል፡፡ ሁሉም ሰው *ጆሮ ሰም* ስላልሆነ ምልክት ቋንቋ ተፈጠረ፡፡ በልሳን ቋንቋ መግባባትም ሆነ በልሳን ቋንቋ መማር *ጆሮ ሰም* ላልሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የማይቻል በመሆኑ፣ *ጆሮ ሰም* ያልሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጆሯቸውን በዐይናቸው ልሳናቸውን ደግሞ በእጃቸው በመተካት የራሳቸውን ድንቅ ቋንቋ ፈጠሩ፡፡ በዕይታ ላይ የተመሠረተ መግባቢያ *ጆሮ ሰም* ባልሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ድንቅ አይደለም፡፡

በመሆኑም በልሳን ቋንቋ የሚግባቡ *ጆሮ ሰም* የሆኑ የሚያደርጉትን የቃለ መጠይቅ መንገድ ተከትለን መስማት ከተሳናቸው ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግ እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ምልክት ቋንቋ በጆሮ ተሰምቶ በአንደበት የሚነገር ሳይሆን በዐይን ተሰምቶ በእጅ፣ በሰውነትና በፊት እንቅስቃሴ/አገላለጽ የሚነገር ስለሆነ መስማት ከተሳናቸው ሰዎች ጋር የሚደረግ ቃለ መጠይቅ የራሱ የሆነ መንገዶች አሉት፡፡

መስማት ከተሳናቸው ሰዎች ጋር የሚደረግ ቃለ መጠይቅ በቃል የሚደረግ ባለመሆኑ ‹‹በምልክት ቋንቋ የሚደረግ መጠይቅ›› ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡ በምልክት የሚደረግ መጠይቅ በዐይን ተሰምቶ በእጅ፣ በፊትና በሰውነት አገላለጽ የሚመለስ በመሆኑ፣ መጠይቅ በሚደረግበት ጊዜ ጠያቂው ከተጠያቂው ፊት በመሆን በሚገባ መተያየት አለባቸው፡፡ ቃለ መጠይቅ በሚደረግበት ቦታም በቂ ብርሃን መኖር አለበት፡፡ መጠይቅ አድራጊው ወይም መጠይቅ የሚደረግለት ሰው ምልክት ቋንቋ የማይችሉ ከሆነ፣ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

መስማት ከተሳነው ግለሰብ ጋር መጠይቅ የሚደረገው በአዳራሽ ውስጥ ከሆነ፣ ግለሰቡ የሚጠየቀው ጥያቄና የሚሰጠው መልስ ለሌሎች በግልጽ ይታይ ዘንድ፣ ጠያቂውና ተጠያቂው ከፍ ያለ ቦታ ላይ መሆን አለባቸው፡፡ በዚህም ጊዜ ከጠያቂውና ከተጠያቂው ጀርባ ብርሃን መኖር የለበትም፡፡ መስማት ከተሳናቸው ሰዎች ጋር መጠይቅ በሚደረግበት ጊዜ ከኋላ ያለ ብርሃን ከፊት ለፊት ያሉ ታዳሚዎችን ዕይታ ስለሚጋርድ መወገድ አለባቸው፡፡

ብዙ ሰዎች መስማት የተሳነውን ግለሰብ የሚጠይቁበት መድረክ ከሆነ፣ ወይም በአንድ ጊዜ ብዙ ጥያቄዎች የሚጠየቅ ከሆነ፣ ምናልባት ሁሉንም ጥያቄዎች አስታውሶ መመለስ አዳጋች ስለሚሆን፣ለግለሰቡ ማስታወሻ የሚይዝለት ሰው ማመቻቸት ወይም ራሱ ማስታወሻ እንዲይዝ በጥያቄዎች መሀል የተወሰነ የጊዜ ክፍተት ማመቻቸት ወይም እያንዳንዱን ጥያቄ ተራ በተራ እንዲመልስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



## መልመጃ ሦስት

ከላይ የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ፣ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶች በደብተራችሁ ከጻፋችሁ በኋላ ለመምህራችሁ በኢምቋግለጹ፡፡

1. መስማት የተሳነው ማለት ምን ማለት ነው?
2. መስማት የተሳናቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚግባቡባቸውን ዘዴዎች ግለጹ፡፡
3. መስማት ከተሳነው ግለሰብ ጋር መጠይቅ ለማድረግ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ምን-ምን ናቸው?
4. መስማት ከተሳነው ግለሰብ ጋር የሚደረግ መጠይቅ ምን ተብሎ ይጠራል?
5. በምንባቡ መሠረት፣ መስማት ለተሳነው ግለሰብ በአንድ ጊዜ ብዙ ጥያቄዎች የሚቀርቡለት ከሆነ፣ ሁሉንም ጥያቄዎች አስታውሶ መመለስ እንዲችል ምን መደረግ አለበት?
6. መስማት ከተሳነው ግለሰብ ጋር መጠይቅ በሚደረግበት ጊዜ ጠያቂውና ተጠያቂው ከፍ ያለ ቦታ እንዲቆሙ የሚደረገው ለምንድን ነው?
7. በልሳን ቋንቋ የሚግባቡ ሰዎች መጠይቅ የሚያደርጉበትን መንገድ ተከትሎ መስማት ከተሳናቸው ጋር መጠይቅ ማድረግ አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድን ነው?
8. መስማት ከተሳነው ግለሰብ ጋር መጠይቅ በሚደረግበት ጊዜ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚ

የሚያስፈልገው መቼ ነው?

# ክፍለ ትምህርት አራት

## ቃለ መጠይቅ

አስረጅ ቃለ መጠይቅ መስማት ከተሳናት ተማሪ ጋር

ጋዜጠኛ ፡ እኔ የመጣሁት ከኢቢኤስ ቴሌቪዥን ድርጅት ነው። አሁን እኔ ለአንቺ ቃለ መጠይቅ አደርግልሻለሁ።

ተርጓሚ ፡ እኔ ሥራ ኢቢኤስ ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ነው። አሁን እኔ አንቺ አብሮ ቃለ ምልልስ ማድረግ ነው።

ኤፍራታ ፡ እሺ እኔ መስማማት።

ተርጓሚ ፡ እሺ እስማማለሁ።

ጋዜጠኛ ፡ ስንተኛ ክፍል ነሽ?

ተርጓሚ ፡ አንቺ ክፍል ስንት?

ኤፍራታ ፡ እኔ ክፍል አሥራ አንድ።

ተርጓሚ ፡አሥራ አንደኛ ክፍል ነኝ።

ጋዜጠኛ ፡ በጣም ጎበዝ ! አሥረኛ ክፍል የት ነው የተማርሽው?

ተርጓሚ ፡ በጣም ጎበዝ ! ክፍል አሥር መማር ቦታ የት?

ኤፍራታ ፡ ጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት

ተርጓሚ ፡ ጥቁር አንበሳ ት/ቤት

ጋዜጠኛ ፡ የአሥረኛ ክፍል መለቀቂያ ፈተና ውጤትሽ ምን ያህል ነው?

ተርጓሚ ፡ አንቺ ክፍል አሥር ነጥብ ስንት?

ኤፍራታ ፡3.4

ተርጓሚ ፡ ሦስት ነጥብ አራት

ጋዜጠኛ ፡ ግሩም .... ግሩም! በጣም ጎበዝ ተማሪነሽ ማለት ነው!?

ተርጓሚ ፡ መገረም!! መገረም!! መገረም!! አንቺ በጣም ጎበዝ!

ኤፍራታ ፡ ምስጋና በጣም፡፡

ተርጓሚ ፡ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ጋዜጠኛ ፡ ለወደፊቱ ምን መሆን ትፈልጊያለሽ?

ተርጓሚ ፡ ወደ ፊት አንቺ ፍላጎት ምን?

ኤፍራታ ፡ አካውንቲንግ፡፡

ተርጓሚ ፡ አካውንታት፡፡

ጋዜጠኛ ፡ በጣም ጥሩ ! ያሰብሽውን እንደምትሆኚ ሙሉ እምነት አለኝ፡፡

ተርጓሚ ፡ በጣም ጥሩ!! እኔ ተስፋ ወደ ፊት አንቺ ሐሳብ መሳካት፡፡

ኤፍራታ ፡ አመሰግናለሁ፡፡

ተርጓሚ ፡ አመሰግናለሁ፡፡

ጋዜጠኛ ፡ እኔም በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## መልመጃ አምስት

ከዚህ በላይ የቀረበውንናሙና መጠይቅ ሁለት ሁለት ሆናችሁ ከተለማመዳችሁ በኋላ፣ ጠያቂና ተጠያቂ ሆናችሁ ከዚህ በታች በተሰጡት አርእስት መጠይቅ አዘጋጅታችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

1. ታካሚና ሀኪም
2. ኮከብ አትሌትና ጋዜጠኛ
3. የሀገር መሪና ጋዜጠኛ
4. ነጋዴና ሸማች
5. አስተማሪና ተማሪ
6. አባትና ልጅ
7. ባልና ሚስት
8. የቢሮ ኃላፊና የጽዳት ሠራተኛ
9. ሌባና ፖሊስ
10. ዕጩ ተመራቂ ተማሪና የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ

# ክፍለ ትምህርት አምስት


## የመወያያ ጥያቄዎች

አምስት አምስት ሆናችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ከተወያያችሁ በኋላ፣ የውይይታችሁን ፍሬ ሐሳብ በቡድን ተወካዮቻችሁ አማካይነት ለክፍል ተማሪዎች በኢምቋ አቅርቡ።

1. በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ቃለ መጠይቆች ለሕዝቡ ምን ጠቃሜታዎች አሏቸው ?
2. ቃለ መጠይቅ አሉታዊ ጎኖች አሉት ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ቃለ መጠይቆች መስማት የተሳናቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችን አካታች ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ? እንዴት?
4. በቃለ መጠይቅ የሚሰበሰብ መረጃ ምን ያህል አስተማማኝ ነው?
5. አንዳንድ ሰዎች ቃለ መጠይቅ ለመደረግ ፍቃደኛ የማይሆኑት ለምን ይመስላችኋል?
6. ቃለ መጠይቅ ከተራ ወሬ የሚለየው በምንድን ነው?

# ምዕራፍ ሦስት

## ባህላዊ ሕክምና



### ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣

* ስለ ባህላዊ ሕክምናና መድኃኒቶች ምንነት በምልክት ቋንቋ ትገልጻላችሁ፤
* የባህላዊ ሕክምና ጠቃሚታና ጉዳቶችን በኢምቋ ትዘረዝራላችሁ፤
* ሰዎች ባህላዊ ሕክምና ለምን እንደሚጠቀሙ ትገልጻላችሁ፤
* የባህላዊ ሕክምናና መድኃኒቶችን፣ በጣት ፊደልና በጽሑፍ ትዘረዝራላችሁ፤
* የጥምር ቃላትና የጥምር ምልክቶች አጠቃቀም ክሂሎታችሁን ታዳብራላችሁ::

## ቁልፍ ምልክቶች



ባህል




ውልቃት



ዝንጅብል



የሆድ ቁርጠት




መፈንከት




ራስን መሳት




ራስ ምታት



ጀሶ



ፋሻ



ነጭ ሽንኩርት



ጤና አዳም



ዳማከሴ



ወጌሻ

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## መመልከትና መግለጽ



ከዚህ በላይ የቀረበውን ስዕል በጥንቃቄ ተመልክታችሁ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በኢምቋ መልሱ።

1. ከዚህ በላይ በተገለጸው ሥዕል ሐኪሙ ወጣቱን ምን እያደረገው ነው?
2. በሥዕሉ ላይ እንደምትመለከቱት ወጣቱ በምን ዓይነት ስሜት ውስጥ ነው?
3. ከወጣቱ ጎንና ጎን ያሉት ሰዎች ወጣቱን ለምን የያዙት ይመስላችኋል?
4. በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ያለውን ሥዕል ተመልክታችሁ ምን እንደ ተረዳችሁ በአጭሩ ግለጹ?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## አንብቦ መረዳት

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በአንቀጽ ተከፋፍላችሁ በማንበብ፣ እያንዳንዱ አንቀጽየያዘውን ፍሬ ነገር ለክፍል ተማሪዎች በኢምቋ አቅርቡ።

### ባህላዊ ሕክምና

ባህላዊ ሕክምና ማለት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የተለያዩ በሽታዎችን ለመከላከልና በበሽታ ከተያዙ ደግሞ ከበሽታው ለመዳን የሚጠቀሙባቸው ልዩ ልዩ ሀገር በቀል የሕክምና ዘዴዎች ነው። በሀገራችን ልዩ ልዩ ባህላዊ ሕክምናዎች አሉ።

በሁሉም ሀገር የሚኖሩ ሕዝቦች የራሳቸው የሆኑ የባሕላዊ ሕክምና ዘዴዎች አሏቸው። ባሕላዊ ሕክምና ከአበውና ከእመው የሚመነጭና እየተላለፈ የሚመጣ በአንጻሩም የኀብረተሰቡን የስልጣኔና የአስተሳሰብ ደረጃ የሚገልጽ የሕክምና ሒደት ነው።

እነዚህ ባህላዊ ሕክምናዎች፣ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ስብራቶችና ውልቃቶችን ለመጠገን፣ ከተለያዩ ሕመሞች ለመፈወስና በሽታዎችንም አስቀድሞ ለመከላከል የምንጠቀምባቸው ናቸው። የቆዳ በሽታዎችን ለመፈወስ የሚደረጉ ባህላዊ ሕክምናዎች አሉ። ለምሳሌ፣የቆዳ መገርጣት፣ የቆዳ በፈላ ውኃ ወይም በእሳት መቃጠል፣ ማድያት፣ ጭርት፣ ቋቁቻ፣ ለማከም የሚደረጉ፣ ወዘተ ናቸው።

በባሕላዊ ሕክምና ከሚካተቱት መካከል ወጌሻ፣ በዋናነት ይጠቀሳል። ወጌሻ አካልን (ለምሳሌ ውልቃት ላጋጠመው እግር፣ እጅ፣ ወገብ፣ ቁርጭምጭሚት፣ ወዘተ፣) ለመጠገን ወይም ውልቃቱንም ለመመለስ የሚደረግ ባሕላዊ የሕክምና ዓይነት ነው። ወጌሻ ያለ ምንም የሕክምና መሣሪያ ባሕላዊ ሐኪሙ ባለው ልምድ የሚያከናውነው ሕክምና በመሆኑ፣ በሕክምናው ሲከወን ከባድ የሆነ የሕመም ስሜት ሊፈጠር ይችላል።ባህላዊ ሕክምና በርካታ ጠቃሚ ጎኖች እንዳሉት የሕክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ። ለምሳሌ ሁለት ትንንሽ ነጭ ሽንኩርት በሁለት ማንኪያ ማር አዝወትሮ መመገብ ከበርካታ በሽታዎች ይከላከላል። ዝንጅብልን በሻይ አፍልቶ መጠጣት ለጉንፋን በሽታዎች መድኃኒትነት አለው። ጤናዳም እንደሰዎች ፍላጎትና የዕድሜ ደረጃ በውኃ፣ በቡና ወይም በሻይ ነክሮ መጠጣት ልዩ ልዩ በሽታዎችን እንደሚከላከልና የደም ዝውውር ሂደትን እንደሚያስተካክል ይታመናል። ዳማከሴ ተቀቅሎ መጠኑን በሚገባ በሚያውቀውና ልምድ ባለው ሰው በመታገዝ የሚጠጣ ከሆነ እንደ ወስፋትና ኮሶ የመሳሰሉትን ጥገኛ ባክቴሪያዎች ከሰውነታችን ለማስወገድ ይረዳል።

በመፈንከትና በልዩ ልዩ አደጋዎች የፈሰሰን ደም ለመተካት፣ ንጽሕናው የተረጋገጠ የበሬ ጉበት መመገብ በጣም ጠቃሚ ነው። በወሊድ ምክንያት ደም የፈሰሳትና አቅሟ የደከመ እናት የፈሰሰ ደሟን ለመተካትና አቅሟን ወደ ነበረበት ለመመለስ እንዲሁም በተገቢው ሁኔታ የጡት ወተት እንዲኖራት አጥሚት መጠጣት በእጅጉ እንደሚረዳት በተለያየ የሀገሪቱ አካባቢዎች የምናየው ተመክሮ ያስረዳል።

የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ነዋሪዎች ወይራ በማጨስ ልዩ ልዩ ተላላፊ በሽታዎችን ሊያስከትሉ የሚችሉ እንደ ዝንብና ቢንቢ የመሳሰሉትን ነፍሳት በማጥፋት ራሳቸውን በነፍሳት አማካይነት ከሚተላለፉ በሽታዎች ይከላከላሉ።

በባህላዊ ሕክምና ከሚስተዋሉ ችግሮች መካከል የቆዳ ሕመሞችን ማከም አንዱ ነው። ሕክምናዎች አንዳንድ ጊዜ ፈዋሽነታቸው ፍቱን ቢሆንም፣ ብዙውን ጊዜ ባሕላዊ ህክምና የተደረገለት ቆዳ ተፈጥሮአዊ ወዙንና መልኩን በመቀየር ለከፋ ጉዳት ሊጋልጥ ይችላል።

የአወሳሰድ መጠንን አለማወቅ፣ መድኃኒቱ የሚወሰድበት ሰዓት በትክክል አለመታወቁ፣ መድኃኒቱ የሚወሰድበት ሁኔታ በግልጽ አለመስፈሩ፣ መድኃኒቱ ከተወሰደ በኋላ ከምን መጠንቀቅና ምን መመገብ እንዳለብን የተገለጸ ነገር አለመኖሩ፣ አዘገጃጀቱና የመድኃኒቱ የቆይታ ጊዜ አለመታወቁ፣ የመድኃኒቱ ማርከሻና ማስታገሻ ተለይቶ አለመገለጹ፣ መድኃኒቱ ከተወሰደ በኋላ የሚያስፈልግ የዕረፍት ጊዜና በዕረፍት ጊዜ የሚወሰዱ መድኃኒቶች ተለይተው አለመገለጻቸው የባህላዊ ሕክምና አሉታዊ ጎኖች ናቸው። ለተለያዩ የሆድ ህመሞች የሚደረገው ባህላዊ ሕክምና የመድኃኒቱ መጠን በውል ስለማይታወቅ መድኃኒቱ በሚወሰድበት ጊዜ ለከፍተኛ የጨጓራና የአንጀት ሕመሞች ሊያጋልጥ ይችላል።

ለተለያዩ የሆድ ሕመሞች የሚደረጉ ባህላዊ ሕክምናዎች የሚታዘዙ መድኃኒቶች በግምት የሚደረጉና ታካሚዎችም በዕድሜ፣ በኑሮ ደረጃ፣ በአመጋገብ የተለያዩ በመሆናቸው ለአንዱ ሰው ፍቱን ነው የተባለ መድኃኒት ሌላውን ሰው ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስበት ወይም ለሞት ሊዳርገው ይችላል።

ወጌሻ ብዙውን ጊዜ ፍቱን እንደሆነ ቢነገርለትም፣ አንዳንድ ጊዜ ውልቃቱን ወይም ስብራቱን በማባባስ ዘላቂ ለሆነ የአካል ጉዳት ሊዳርግ ይችላል።

ሁሉም ባህላዊ ሕክምናዎች ጎጂ ናቸው ብሎ መናገር ባይቻልም፣ በአብዛኛው ለውስጥ ደዌ የሚደረጉ ባሕላዊ ሕክምናዎች ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው እንደሚያመዝን ይገመታል።

ሰዎች ወደ ባህላዊ ሕክምና እንዲያዘነብሉ የሚያደርጓቸው ልዩ ልዩ ምክንያቶች አሉ። አንዱ የግንዛቤ ችግር ነው፣ የገንዘብ እጥረትም ሊጠቀስ ይችላል። በተለያዩ ባሕላዊ እምነቶችና አመለካከቶች መያዝ፣ በዘመናዊ ሕክምና ላይ እምነት ማጣት በተጨማሪነት ይጠቀሳሉ። እነዚህንና መሰል በባህላዊ ሕክምና የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ ባህላዊ ሕክምናዎችን በምርምር ማሳደግ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም የሰው ልጅ በእውቀቱ እየዳበረ የሳይንሳዊ ውጤቶችን ተጠቃሚነቱ እያደገ ስለመጣ የባህላዊ ሕክምናዎች ተፈላጊነት እየተቀነሰ በምትካቸው ፍቱንነታቸው በሳይንስ የተረጋገጡ የሕክምና ዘዴዎች እየጎለበቱ መጥተዋል። በመሆኑም ባህላዊ ሕክምናዎችን በምርምር ማሳደግ አሊያም ፍቱንነታቸው በሳይንስ የተረጋገጡ ሕክምናዎችንና መድኃኒቶችን በመጠቀም በባህላዊ ሕክምናና በባህላዊ መድኃኒቶች አማካይነት የሚከሰቱ ችግሮች ሊቀረፉ ያስፈልጋል።

*(ምንጭ፣ መድኃኒት በኪሴ ከሚለው መጽሐፍ ተሻሽሎ የተወሰደ።)*





## መልመጃ አንድ

ከላይ የቀረበውን ምንባብ በጽሞና አንብባችሁ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ በጽሁፍ ከሰጣችሁ በኋላ በምልክት ቋንቋ ለመምህራችሁ ግለጹ።

1. ባሕላዊ ሕክምና ምንድን ነው?
2. ባሕላዊ ሕክምና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ምን-ምን ናቸው?
3. ባሕላዊ ሕክምና ምን-ምን ጠቃሚታዎች አሉት?
4. ሰዎች በባሕላዊ ሕክምና የሚታከሙባቸው ምክንያቶች ምን-ምን ናቸው ?
5. በምንባቡ ውስጥ ስንት ዓይነት የባሕላዊ ሕክምና ዓይነቶች ተዘርዝረዋል?

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### የኢምቋ ጥምር ምልክቶችና የአማርኛ ጥምር ቃላትን መግለጽ

የኢምቋ ጥምር ምልክቶችና የአማርኛ ጥምር ቃላት የሚገለጹባቸው መንገዶች።

በልሳን ቋንቋ ሁለት ቃላት ተጣምረው አንድ ከሁለቱም ቃላት የተለየ ትርጉም ያለው ቃል ይፈጥራሉ። በምልክት ቋንቋ ሁለት ምልክቶች ተጣምረው አንድ ከሁለቱም ምልክቶች የተለየ ትርጉም ያለው ምልክት ይፈጥራሉ።

የአማርኛ ቋንቋ የጥምር ቃላት ምሳሌ፡

አየር + ወለድ

ብረት + ምጣድ

እግር + ብረት

ከዚህ በላይ የተገለጹት የአማርኛ ጥምር ቃላት እንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ቃላት ይኑራቸው እንጂ፣ የያዙት ሐሳብ ወይም መልዕክት አንድ ነው። በመሆኑም እነዚህን ቃላት በምልክት ቋንቋ ለመግለጽ ወይም ለመተርጎም የምንጠቀመው ምልክቶች ብዛት የተለያየ ነው።

ምሳሌ

አየር ወለድ ለሚለው ጥምር ቃል ወታደር የሚለውን አንድ ምልክት በመጠቀም ይገለጻል።

ብረት ምጣድ ለሚለው ጥምር ቃል ብረትና ሳሕን ወይም ምጣድ የሚሉትን ሁለት ምልክቶችን በመጠቀም ይገለጻል።

እግር ብረት የሚለው ጥምር ቃል የሚያመለክተው የእግር ማሰሪያ ብረት እንደመሆኑ እግር፣ ማሰርና

ብረት (ሰንሰለት) የሚሉትን ሦስት ምልክቶችን በመጠቀም ይገለጻል። በመሆኑም የአማርኛ ጥምር ቃላት በኢምቋ በአንድና ከዚያ በላይ በሆኑ ምልክቶች ሊገለጹ ይችላሉ።

ተጨማሪ ምሳሌዎች፣

ሥነሥርዓት = ደንብ

ሥነምግባር = ጸባይ

እኩለ ለሊት = የሌሊቱ አጋማሽ

ቤተ መጻሕፍት = ላይብረሪ

ነገረ ፈጅ = ጠበቃ

እግረሙቅ = የእግር ማሰሪያ ብረት

ፊር ቀዳጅ = የመጀመሪያ

ግንባር ቀደም = መሪ

ከዚህ በላይ የተገለጹት ጥምር ቃላትና ምሳሌያዊ ንግግሮች ከ"እግረ ሙቅና" "እኩለ ለሊት" በስተቀር ሌሎች በአንድ ምልክት የሚገለጹ ናቸው። ይህ ማለት አንድን ምልክት ከመተርጎም ወይም ከመግለጽ በፊት ጥምር ቃሉ የያዘውን ሐሳብ ወይም መልዕክት መረዳት ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ የሰማናቸውን ቃላት ቃል በቃል ለመተርጎም ወይም በምልክት መግለጽ ቃሉ ትርጉም የለሽ ከመሆኑም ባሻገር መልዕክት ተቀባዩን (አድማጩን) ግራ ሊያጋባው ይችላል።

ለምሳሌ

"አጉራ ዘለል" የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር ምን ተብሎ ወደ ኢምቋ ሊተረጎም ወይም ሊገለጽ እንደሚችል እናስብ።

"አንገተ ሰባራ" የሚለውን ምሳሌያዊ ንግግር ደግሞ ቃል በቃል ለመተርጎም ወይም ለመግለጽ መሞከር ምናልባት "የተሰበረ አንገት" ወደሚል የተዛባ ትርጉም ሊያመራ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል።

ከዚህ በላይ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡት ጥምር ቃላት ሁለት ሁለት ቃላትን ይያዙ እንጂ የሚወክሉት አንድ ነገር ነው። በምልክት ቋንቋም ሁለት ምልክቶች ተጣምረው አንድን ነገር የሚወክሉበት ጊዜ በርካታ ነው።

የኢምቋ ጥምር ምልክቶች ምሳሌ

ባሪያ + መክተፍ = ሽንኩርት

ቆርቆሮ + ጀበና = ማንቆርቆሪያ

ቀይ + መክተፍ = ቲማቲም

ወንድ + ቀለበት = ባል

ሴት + ቀለበት = ሚስት

ቀይ + መጻፍ = እስኪርብቶ

ባል + መሞት + ሴት = መበለት

በሌላ በኩል በኢምቋና አማርኛ ጥምር የሆኑ ምልክቶችና ቃላት አሉ። እነዚህ ምልክቶች እንዳላቸው ጥምር ቃላት በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ምልክቶች ይገለጻሉ።

ምሳሌ ፦ ጥቁር:ሰሌዳ፣

ነጭ:ሰሌዳ፣

ቤተ:መንግሥት

ከዚህ በላይ የተገለጹት ጥምር ቃላት በኢምቋም በተመሳሳይ በጥምር ምልክት የሚገለጹ ናቸው።

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ጥምር ቃላትና ጥምር ምልክቶችን ምሳሌ በማድረግ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በደብተራችሁ ከጻፋችሁ በኋላ፣ በኢምቋ ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. የጥምር ቃላትና የጥምር ምልክቶች ተመሳሳይነት ምንድን ነው ?
2. የጥምር ቃላትና የጥምር ምልክቶች ልዩነት ምንድን ነው?
3. የአማርኛ ጥምር ቃላትን በኢምቋ በሚገለጽበት ጊዜ የምልክቶች ብዛት የሚለያየው ለምንድን ነው?
4. አንድ መስማት የተሳነው ግለሰብ የአማርኛ ጥምር ቃላት በሚተረጎምበት ጊዜ ግራ ሊገባው የሚችለው ምን ሲሆን ነው?
5. የአማርኛ ጥምር ቃላትን በሚገባ በኢምቋ ለመተርጎም ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

## መልመጃ ሦስት

ከላይ የቀረበውን የኢምቋ ጥምር ምልክቶችና ጥምር የአማርኛ ቃላት ምሳሌ መሠረት በማድረግ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ ሠርታችሁ በክፍል ውስጥ በኢምቋ አሳዩ።

1. አምስት የአማርኛ ጥምር ቃላትን ፈልጋችሁ በማምጣት በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጹ አሳዩ።
2. አምስት የኢምቋ ጥምር ምልክቶችን ፈልጋችሁ በማምጣት በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጹ አሳዩ።

3. ጥምር ቃላት ከሐረግ በምን እንደሚለዩ በምሳሌ አስደግፋችሁ በኢምቋ ግለጹ?
4. ጥምር ምልክት ከሁለት ምልክቶች በምን እንደሚለይ በምሳሌ አስደግፋችሁ አሳዩ?
5. ጥምር ምልክቶች የሚፈጠሩበት ምክንያት ምንድን ነው?

## መልመጃ አራት

የሚከተሉትን ጥምር ምልክቶች ከትክክለኛ አገላለጻቸው ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መበለት | ሀ. ነጭ + ጸጉር |
| 2. ሽቦ | ለ. ደረጃ + መዘርጋት |
| 3. አስፓልት | ሐ. ነጭ + ባሪያ + መክተፍ |
| 4. ሽበት | መ. ባል + መሞት + ሴት |
| 5. ነጭ ሽንኩርት | ሠ. ቆርቆሮ + ገመድ |
| 6. መድረክ | ረ. ጥቁር + ንጹሕ |

## መልመጃ አምስት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላት ትርጉማቸውን በጥንቃቄ ካጠናችሁ በኋላ፣ በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጹ በክፍል ውስጥ አሳዩ።

1. ራስን መሳት
2. ራስ ምታት
3. በምች መመታት
4. ጤናዳም (ጤና አዳም)
5. ፋሻ
6. ወጌሻ
7. ውልቃት

8. ስብራት
9. ዳማከሴ
10. ዝንጅብል

# ክፍለ ትምህርት አራት

## ሐሳብን በኢምቋ የመቀበልና የመግለጽ ክሂል

### ጭውውት

ርእስ፤ *መጋጨት*

በጥንድ እየሆናችሁ ከዚህ በታች የቀረበውን ጭውውት ከተለማመዳችሁ በኋላ፤ ተራ በተራ እየወጣችሁ ለክፍል ተማሪዎች አሳዩ::

ሁለት ተማሪዎች አንዱ ከግራ ወደ ቀኝ ሁለተኛው ደግሞ ከቀኝ ወደ ግራ ሲሄዱ ይታያል:: በመሃል ሁለቱ ተማሪዎች ትከሻ ለትከሻ ይገጫጫሉ::

ተማሪ አንድ፤ ለምን ገጨኸኝ? እያየህ አትሄድም?

ተማሪ ሁለት፤ እኔነኝ የገጨሁህ?! ራስህ እያየህ አትሄድም?

ተማሪ አንድ፤ እኔ አላየሁህም አንተ ለምን እያየህ አትሄድም?

ተማሪ ሁለት፤አንተ እያየህ የማትሄድ ከሆነ፤ የማን ጥፋት ነው?

ተማሪ አንድ፤ ምን?

ተማሪ ሁለት፤ማነው የተጋጨው? ማለት፤ እኔ አንተን ገጨሁህ?፤ አንተ እኔን ገጨኸኝ፤? ወይስ ሁለታችንም እኩል ተጋጨን?

ተማሪ አንድ፤ ይቅርታ! ሁለታችንም እኩል የተጋጨን ይመስለኛል::

ተማሪ ሁለት፤ ለኔም ይቅርታ አድርግልኝ::

ተጨባብጠው ይለያያሉ::

# ምዕራፍ አራት

## ትምህርት




ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣

* የትምህርት ምንነት በኢምቋ ትገልጻላችሁ፤
* መደበኛና ኢ-መደበኛ ትምህርት ሥልቶች በኢምቋ ትለያላችሁ፤
* በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት የሚካተቱ በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ አጠቃላይ ምልክቶችን በኢምቋ ትዘረዝራላችሁ፤
* ትምህርት ለሀገር ዕድገት ያለው ጠቃሜታ በኢምቋ ትገልጻላችሁ፤
* መስማትየተሳናቸውተማሪዎችንየማስተማሪያሥልቶችንበኢምቋትተነትናላችሁ፤አዳዲስ ምልክቶችን ትለያላችሁ፣
* የኢምቋ ነጠላ ስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር የመቀየር ክሂሎታችሁን ታዳብራላችሁ::


## ቁልፍ ምልክቶች



አማርኛ




እንግሊዝኛ



ሒሳብ




ሳይንስ




ኬሚስትሪ




ባይሎጂ



ጂኦግራፊ




ፊዚክስ




አካውንቲንግ




ፍልስፍና




ድሮይንግ




ኢኮኖሚክስ



ሥነ ልሳን




ልዩ ፍላጎት



ስፖርት



ሥነ ዜጋ




## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መመልከትና መግለጽ



ከዚህ በላይ የቀረበውን ሥዕል ተመልክታችሁ ከሥዕሉ ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ተማሪዎች በኢምቋ ግለጹ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በኢምቋ መልሱ::

1. ትምህርት ማለት ምን ማለት ነው?
2. አንድ ሰው መማር የሚጀምረው መቼ ነው?
3. ከላይ የቀረበው ሥዕል የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው ?

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## አንብቦ መረዳት

ከዚህ በታች የቀረቡትን የታላላቅ ሰዎች አባባሎች አንብባችሁ፣ ሊያስተላልፉ የፈለጓቸውን ሐሳቦች ለክፍል ተማሪዎች በኢምቋ አቅርቡ::

### ስለ ትምህርት ምንነትና ጠቃሚታ ከታላላቅ ሰዎች አንደበት

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስካለንበት ጊዜ ድረስ የኖሩ ታላላቅ ሰዎች ስለ ትምህርት ምንነትና ጠቃሜታዎቹ የተናገሩትን ስንመለከት ለትምህርት ያለንን አዎንታዊ አመለካከት በእጅጉ ያዳብረዋልና ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከታቸው::

ስዊዘርላንዳዊ የሥነ ልቡና ባለሙያና ፈላስፋ፣ ጄን ፒያጌት (1896 — 1980) ስለ ትምህርት እንዲህ ይላል፣ "በትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ትምህርቶች ዋነኛ ግባቸው ያለፉት ውልዶች ያደረጉትንና የተማሩትን መደጋገም ብቻሳይሆን፣ ተማሪዎች አዳዲስ ነገሮችን መሥራትና ማበልፀግ እንዲችሉ ብቁ ማድረግ መሆን አለበት::"

አናቶሊ ፍራንሲስ የተባለ ከ1844-1924 የኖረ ፈረንሳዊ ጸሐፊና ገጣሚ ስለ ትምህርት እንዲህ ይላል፣ "ትምህርት ማለት ምን ያህል ሸምድደን በአእምሮአችን ይዘነዋል፣ አልያም ምን ያህል የመጽሐፍቱን ክፍሎች አንብበናል ሳይሆን፣ የምናውቀውንና የማናውቀውን ምንያህል መለየት ችለናል የሚለውን መመለስ መቻል ነው::"

ደቡብ አፍሪካዊ የነጻነት ታጋይና መሪ ኔልሰን ማንዴላ (1918-2013) ደግሞ እንዲህ ይላሉ፣ "ትምህርት እጅግ ኃይለኛ ዓለምን የመቀየሪያ መሣሪያ ነው::"

ግሪካዊ የሒሳብ ሊቅና ፈላስፋ የነበረው ፕሌቶ (424-348 ዓ.ዓ) ትምህርትን እንዲህ ይገልጸዋል "የትምህርት ዋናው አላማው ውበትን እንዴት መውደድ እንደምንችል ማስተማር ነው::"

አሜሪካዊው የነጻነት ታጋይ ማርቲን ሉተር ኪንግ (1929-1968) ትምህርትን በማስመልከት እንዲህ ይላል፣ “የትምህርት ዋናው ተግባር አንድን ሰው እንዴት በትኩረትና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ማሰብ እንደሚችል ማድረግ ነው። የተማረ አቅምንና ምሉዕ ምግባር መፍጠር የትክክለኛ ትምህርት ግብ ነው።”

በትውልድ እስራኤላዊ በዜግነት አሜሪካዊ የሆነው የፊዚክስ ሊቅና የአቶሚክ ቦምብ ፈጣሪ አልበርት አንስታይን (1879-1955) የትምህርት እንዲህ ይገልጸዋል፣ “ትምህርት ማለት አንድ ሰው በትምህርት ገበታው ላይ ከተማራቸው ያልረሳው ክፍል ነው።”

ፓብሎ ፍሬይር የተባለ ብራዚላዊ መምህርና ፈላስፋ ትምህርትን እንዲህ ይገልጸዋል፣ “ትምህርት ነፃነት ነው።”

የሥነ ልቡና ተመራማሪና ፈላስፋ የሆነው ጆን ዲዌይን (1859-1952) ስለ ትምህርት እንዲህ በማለት ገልጾዋል፣ “ትምህርት ለሕይወት መዘጋጃ መሣሪያ አይደለም፤ ይልቁንም ትምህርት በራሱ ሕይወት ነው እንጂ።” ይህ ፈላስፋ የትምህርትን ጠቃሜታ ሲያጠናክር እንዲህ ይላል፣ “ትምህርት ማለት ወርቃማውን የነፃነት በር መክፈቻ ቁልፍ ነው።”

አየርላንዳዊ ጸሐፊና ገጣሚ፣ ኦስካር ዊልድ(ከ1854 - 1900) “አጠቃላይ የትምህርት ግቡ መስታወቶችን ወደ መስኮቶች መቀየር ነው።”

ጋዜጠኛ ሲድኒ ጄ. ሀሪስ (ከ1917 — 1986) “የትምህርት ዓላማ ዝግ የሆነን ጭንቅላት ክፍት ማድረግ ነው።”

ፖለቲከኛና ጸሐፊ፣ ኤማ ጎልድማን (ከ1869- 1940) ስለ የዘመናችን የትምህርት አሰጣጥ አስመልክታ እንዲህ ትላለች፣ “አብዛኞቹ የዘመናችን ትምህርት ሥርዓቶች ስኬታማ ያልሆኑ ናቸው። ምክንያቱም አብዛኞቹ የትምህርት ሥርዓቶች አዳጊዎች ዕፀዋቱን እንዲቀጡፉ እንጂ ተክለው እንዲያሳድጉ አያስተምሯቸውም።”

*(ከልዩ ልዩ ምንጮች የተወሰደ)*



## መልመጃ አንድ

ከላይ የቀረበውን ምንባብ በጥንቃቄ አንብባችሁ፣ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በኢምቋ መልስ ስጡ::

1. በምንባቡ ውስጥ ያልተገለጹ የትምህርት ጠቃሚታዎችን ዘርዝራችሁ በደብተራችሁ ከጻፋችሁ በኋላ ለመምህራችሁ በኢምቋ አሳዩ::
2. ሰዎች ለሕይወታቸው ጠቃሚ ትምህርት ሊያገኙ የሚችሉባቸው ሥፍራዎች የት እንደሆኑ ግለጹ::
3. ለሰዎች የተሳሳተ መረጃ በመስጠት የሰዎችን ደኅንነት ሊያውኩ የሚችሉ ሥፍራዎች የት የት ናቸው?
4. የኢመደበኛና መደበኛ ትምህርት ተመሳሳይነታቸውንና ልዩነታቸውን ግለጹ::
5. ኢመደበኛ ትምህርት እንደ አካባቢውና እንደ የአካባቢው ነዋሪዎች የአኗኗር ዘይቤ የተለያየ ነው የሚለውን ሐሳብ በምሳሌ ግለጹ::

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በላይ የቀረቡትን የታላላቅ ሰዎች አባባሎች ካነበባችሁ በኋላ፣ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በኢምቋ መልሱ::

1. ከዚህ በላይ ካነበባችኋቸው አባባሎች በጣም የወደዳችሁት አባባል የትኛው ነው? ለምን እንደወደዳችሁት ግለጹ::
2. ከዚህ በላይ ከቀረቡት አባባሎች ያልወደዳችሁት አባባል የትኛው ነው? ለምን እንዳልወደዳችሁት ግለጹ::
3. ብራዚላዊው ፈላስፋ ፓብሎ ፍሬይር “ትምህርት ነጻነት ነው” ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ደቡብ አፍሪካዊው የነጻነት ታጋይ የነበሩት ኔልሰን ማንዴላ “ትምህርት ዓለምን መቀየሪያ መሣሪያ ነው” ያሉት ለምንድን ነው?
5. ጆን ዲዌይን “ትምህርት ሕይወት ነው” ያለው ለምን ይመስላችኋል?
6. ሲዲኒ ጄ. ሀሪስ “የትምህርት አላማ ዝግ የሆነን ጭንቅላት ክፍት ማድረግ ነው::” ሲል ምን ማለት ፈልጎ እንደሆነ ግለጹ::

# ክፍለ ትምህርት አራት

## የኢምቋ ነጠላ ስሞችንና ግሶችን ወደ ብዙ ቁጥር የመቀየሪያ ዘዴዎች።

በኢምቋ ነጠላ ስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር የመቀየሪያ የተለያዩ ሥልቶች አሉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው፤ ብዙ የሚለውን ምልክት ከተገለጸው (ከተጠቀሰው) ስም ቀጥሎ ወይም አስቀድሞ በማስገባት፣ ምልክቱን ወይም አደራረጉን በመደጋገም፣ የእጅ እንቅስቃሴውን ወደ የተለያዩ አቅጣጫዎች በማወዛወዝ፣ ወዘተ።

### ሀ. ብዙ የሚለውን ምልክት ከተጠቀሰው ስም ቀጥሎ ወይም አስቀድሞ በማስገባት ወደ ብዙ ቁጥር የሚቀየሩ ምልክቶች ምሳሌ፣

ተማሪ + ብዙ = ተማሪዎች

ሰው + ብዙ = ሰዎች

ታክሲ + ብዙ = ታክሲዎች

መጽሐፍ + ብዙ = መጻሕፍት

መንገድ + ብዙ = መንገዶች

### ለ. ምልክቱን ወይም አደራረጉን በመደጋገም የሚገለጹ ምልክቶች ምሳሌ፣

ሰበረ + ሰበረ + ሰበረ + ሰበረ = ሰባበረ

ቀደደ + ቀደደ + ቀደደ + ቀደደ = ቀዳደደ

ቆረጠ + ቆረጠ + ቆረጠ + ቆረጠ = ቆራረጠ

ፈለጠ + ፈለጠ + ፈለጠ + ፈለጠ = ፈላለጠ

### ሐ. የእጅ እንቅስቃሴውን በመደጋገም ወደ ብዙ ቁጥር የሚቀየሩ ምልክቶች ምሳሌ፣

**ዛፍ** የሚለው ምልክት ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ የእጅ እንቅስቃሴው ሲደጋገም ብዙ ዛፎችን ወይም ደን/ጫካ/ የሚለውን ምልክት ያመለክታል።

**ልጅ** የሚለው ምልክት ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ የእጅ እንቅስቃሴው ሲደጋገም ልጆች የሚለውን ምልክት ያመለክታል።

### መ. በአንድ ስም የሚጠሩ ሆነው በዓይነትና በመጠን የሚለያዩ ነገሮችን ለመግለጽ የሚያገለግሉ መንገዶች።

በአንድ ምድብ የሚመደቡ ወይም በአንድ ስም የሚጠሩ ሆነው የተለያየ መጠንና ቅርጽ ያላቸውን ነገሮች ለመግለጹ ከላይ ከተጠቀሱት ወደ ብዙ ቁጥር መቀየሪያ ሥልቶች ባሻገር **ልዩ** የሚለውን ምልክት ከተጠቀሰው ስም ለጥቆ ወይም ቀድሞ ደጋግሞ መጠቀም ያስፈልጋል።

ምሳሌ

ብረት + ብዙ = ብረቶች

ብረት + ብዙ + ልዩ + ልዩ = ልዩ ልዩ ብረቶችን ወይም ብረታብረት የሚለውን ምልክት ይገልጻል።

ጨርቅ + ብዙ = ብዙ ጨርቅ ወይም ጨርቆች

ጨርቅ + ብዙ + ልዩ + ልዩ = ልዩ ልዩ ጨርቆችን ወይም ጨርቃጨርቅ የሚለውን ምልክት ይገልጻል።

## መልመጃ ሦስት

ከዚህ በላይ የቀረበውን ነጠላ ስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር የመቀየር ሥልቶችን ምሳሌ በማድረግ፣ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በኢምቋ መልሱ።

1. ብዙ የሚለውን ምልክት በመጠቀም ወደ ብዙ ቁጥር የሚቀየሩ አምስት ምልክቶችን ሠርታችሁ አሳዩ።
2. ምልክቱን በመደጋገም ወደ ብዙ ቁጥር የሚቀየሩ አምስት ምልክቶችን ሠርታችሁ አሳዩ።
3. የእጅ እንቅስቃሴውን በመደጋገም ወደ ብዙ ቁጥር የሚቀየሩ አምስት ምልክቶችን ሠርታችሁ አሳዩ።
4. ቅመማቅመም የሚለው ምልክት በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጽ አሳዩ።
5. ጥራጥሬ የሚለው ምልክት በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጽ አሳዩ።
6. የበግ መንጋ የሚለው ምልክት በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጽ አሳዩ።
7. እቅፍ አበባ የሚለው ምልክት በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጽ አሳዩ።
8. የድንጋይ ክምር የሚለው ምልክት በኢምቋ እንዴት እንደሚገለጽ አሳዩ።

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## ባለቤትና ተሳቢ አመልካች ምልክቶች

ወለድኩ (አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ፆታው ያልተገለጸ)

ይህ ምልክት "እኔ" እና "መውለድ" በሚሉ ሁለት ምልክቶች ይገለጻል::

ውለጂ (ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ዕንስታይ ፆታ)

ይህ ምልክት "አንቺ"፣"ወደፊት"፣ እና "መውለድ" በሚሉ ሦስት ምልክቶች ይገለጻል።

ውለዱ (ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ፆታው ያልተገለጸ)

ይህ ምልክት "እናንተ"፣"ወደፊት" እና "መውለድ" በሚሉ ሦስት ምልክቶች ይገለጻል::

ተወለደ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታ)

ይህ ምልክት በኢምቋ "እሱ" እና "መውለድ" በሚሉ ሁለት ምልክቶች ይገለጻል::

ተወለደች (ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ዕንስታይ ፆታ)

ይህ ምልክት በኢምቋ "እሷ" እና "መውለድ" በሚሉ ሁለት ምልክቶች ይገለጻል::

ማዋለድ

ተግባርን የሚገልጽ በመሆኑ ይህን ምልክት በኢምቋ "መርዳት" እና "መውለድ" በሚሉት ሁለት ምልክቶች ይገለጻል

አዋላጅ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ፆታው ያልተገለጸ)

ተግባርን የሚገልጽ ምልክት በመሆኑ ይህ ምልክት በኢምቋ "መውለድ" እና "መርዳት" ወይም "መውለድ" "መንከባከብ" እና "ጨራሽ" በሚሉ ሦስት ምልክቶች ይገለጻል

ትወልዳለች (ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ዕንስታይ ፆታ)

ይህ ምልክት ወደፊት የሚሆነውን የሚገልጽ በመሆኑ፣ "እሷ"፣ "ወደፊት" እና "መውለድ" በሚሉ ሦስት ምልክቶች ይገለጻል::

ይወልዳሉ (ሦስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ፆታው ያልተገለጸ)

ይህ ምልክት "እነሱ" "ወደፊት" እና "መውለድ" የሚሉትን ሦስት ምልክቶች በመሥራት ይገለጻል::

እንወልዳለን (አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር ያታው ያልተገለጸ ይህ ምልክት"እኛ" እና "መውለድ" የሚሉትን ምልክቶች ደጋግሞ መሥራት ወዘተ::

## መልመጃ አራት

ከዚህ በላይ የቀረበውን ምሳሌ መሠረት፣ በማድረግ የሚከተሉት ምልክቶችን የሚወክሉ ቃላት ትክክለኛ የኢ-ምቋ ምልክቶቻቸውን አሳዩ::

1. ቆጠብኩ
2. ቆጠብን
3. ቆጠበ
4. ቆጠቡ
5. ቆጠበች
6. ቆጣቢ

## ክፍለ ትምህርት ስድስት


### በኢምቋ ሐሳብን የመቀበልና የመግለጽ ክሂል

በቡድን ሆናችሁ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሐሳቦች ላይ አጭር ጭውውት/ተውኔት ሰርታችሁ ለክፍል ተማሪዎች በኢ-ምቋ አሳዩ::

1. የትምህርት ዕድል ያላገኘ ወጣት የሚያጋጥመውን ችግሮች የሚያሳይ ጭውውት/ተውኔት ሠርታችሁ በክፍል ውስጥ በኢ-ምቋ አቅርቡ
2. በኢ-መደበኛ የትምህርት ዘዴ የሚገኝ እውቀት በተግባር የሚያሳይ ጭውውት/ተውኔት ሠርታችሁ በክፍል ውስጥ በኢ-ምቋ አቅርቡ::
3. መደበኛ የትምህርት ሥርዓት ለግለሰብ፣ ለቤተሰብና ለሀገር እድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ የሚያሳይ ጭውውት/ተውኔት ሠርታችሁ በክፍል ውስጥ በኢ-ምቋ አቅርቡ::
4. ከተለያዩ ደላሎች ማታለልና የ3ደኛ ግሬቶች ራሳቸውን ጠብቀው ትምህርታቸውን በከፍተኛ ውጤት ያጠናቀቀች ወጣት በመጨረሻ የምታገኘውን ደስታ የሚያሳይ ጭውውት/ተውኔት ሠርታችሁ በክፍል ውስጥ በኢ-ምቋ አቅርቡ::

# ምዕራፍ አምስት

## ኢትዮጵያዊነት




ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፣

* የኢትዮጵያዊነት ምንነት በኢምቋ ትገልጻላችሁ፤
* ስለ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦች እኩልነት በኢምቋ ትዘረዝራላችሁ፤
* የብሔር ብሔረሰብ ስሞችን በኢምቋና በጣት ፊደላት፤
* የሥራ ቋንቋና የብሔረሰብ ቋንቋ ሚና ትለያላችሁ፤
* የቋንቋዎችን እኩልነት በኢምቋ ትገልጻላችሁ፤
* የአዳዲስ ምልክቶች አጠቃቀም ክሂሎታችሁን ታዳብራላችሁ።


## ቁልፍ ምልክቶች



ኢትዮጵያዊነት



አርበኛ



ማንነት


እንቆቅልሽ


ጀግንነት


ድፍረት


ቅኝ ግዛት




# ክፍለ ትምህርት አንድ

## መመልከትና መግለጽ

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በኢምቋ ያቀርቡላችኋል መምህራችሁን በጽሞና ተከታተሏችሁ ለጥያቄዎቹ በኢምቋ መልስ ስጡ፡፡

1. ኢትዮጵያዊነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ኢትዮጵያዊነት የሚገለጽባቸው መንገዶች ምን-ምን ናቸው?
3. ከዚህ በታች ያለው ሥዕል የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው?








## ክፍለ ትምህርት ሁለት

### ውይይት

መምህር፡ ተማሪዎች ዛሬ ስለ ኢትዮጵያዊነት ምንነትና ጠቃሜታው እንወያያለን፤ ውይይቱን የሚደረገው በጥያቄና መልስ ስለሆነ የነቃ ተሳትፎ እንድታደርጉ ይጠበቃል፡፡

ተማሪዎች፡ እሺ መምህር በማለት በአንድ ድምጽ መለሱ፡፡

መምህር፡ ኢትዮጵያዊነት ማለት ምን ማለት ነው?

እንዳለ፡ ኢትዮጵያዊነት ማለት እርስ በርስ መዋደድና መከባበር ከመሆኑ በተጨማሪ የማንነታችን መገለጫ ነው፡፡

መምህር፡ እንዳለ የሰጠው ሐሳብ ግልጽ የሚያደርግልኝ አለ?

ሙሉነሽ፡ ኢትዮጵያዊነት ማለት እርስ በርስ መዋደድ ነው ሲባል ያለውን ማካፈል፣ አብሮ መብላትንና መጠጣትን፣በችግርና በደስታ ጊዜ መረዳዳትን ወዘተ የሚያጠቃልል

ነው::

በርሔ: የማንነታችን መገለጫ ነው ሲባል ደግሞ የራሳችን የሆነ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች፣ ትውፊትና አመለካከት ያለን ዜጎችመሆናችን የሚገልጽ ነው::

መምህር: በጣም ጥሩ!! መከባበር ሲባልስ?

ሙራድ: መከባበር በዕድሜ ታላላቅ የሆኑትን ከማክበር የሚጀምር ሲሆን በመቀጠል ማንኛውንም ሰው በዕድሜው፣ በጾታው፣ በብሔሩ፣ በሃይማኖቱ ባለበት የአካል ጉዳት፣ ወዘተ፣ መገለልና መድልዖ ሳይደረግበት በመከባበር አብሮ መኖርን የሚገልጽ ነው::

መምህር: ሌላ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ የሚነግረኝ አለ ?

ሀወኒ : የሀገርን ክብር መጠበቅና ሀገርን ከጥቃት መከላከል የኢትዮጵያዊነት መገለጫዎች ናቸው::

ቢኒያም: ሀወኒ ከመለሰችው በተጨማሪ የሀገር ድንበርን መጠበቅና ማስከበር የኢትዮጵያዊነት መገለጫዎች ናቸው::

መምህር: እንዴት ?

አኖሌ: ኢትዮጵያ ሉአላዊነቷን/ክብሯን/፣ በሀገሪቷ የሚነገሩ ልዩ ልዩ ቋንቋዎቿ ተከብረውና ተጠብቀው የኖሩት ሕዝቧ ከጥንት ጀምሮ ባለው ብሔራዊ ስሜት ምክንያት ነው::

መምህር: እንደዚህ ዓይነት ሀገራዊ ፍቅር በሌሎች ሀገሮች የለም ወይ?

ጫላ: የለም!! እንኳን በአፍሪካ ሀገራት አሁን በኃያልነቷ የምናውቃት አሜሪካ ለበርካታ ዓመታት በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስትማቅቅ ኖራለች::

መምህር: አሜሪካንን ጨምሮ አብዛኞቹ የዓለም ሀገራት በቅኝ ግዛት የመገዛታቸው ምክንያት ምንድን ነው?

ጫልቱ: የሀገር ፍቅር አለመኖር ይመስለኛል:: ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው መስዋዕት መሆን እንደመታደል ስለሚያዩት ለነፍሳቸው አይሣሱም::

መምህር: ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት አለመያዟ ምን-ምን ፋይዳዎችን አስገኝቶላታል

አዚዛ: አሁን የምንግባባበት ቋንቋ ጨምሮ ባህላችን፣ አመለካከታችን፣ ትውፊታችን፣ ታሪካችን እንዲጠበቅ በየትኛውም ሀገር ኮራ ብለን እንድንሠራና እንድንኖር አስችሎናል::

መምህር: የሀገር ፍቅር አለመኖር የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?

ግሩም: የሀገር ፍቅር አለመኖር ለውጭ ጠላቶች በማጋለጥ በኢኮኖሚ፣ በባህል፣ በማኅበራዊ ኑሮ፣ በአመለካከትና በአስተሳሰብ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል::

ክፍሎም፡ በአጠቃላይ የሀገር ፍቅር አለመኖር ማንነትን ያቃውሳል። በቅኝ ግዛት የተያዙ

አብዛኞቹ ሀገራት የራሳቸው ቋንቋ፣ባህልና አመለካከት ስለሌላቸው ማንነታቸው

ተቃውሶ በማንነት ፍለጋ ላይ ናቸው።

መምህር፡ ይህን የመሰለ የሀገር ፍቅር ሀገራችን ይበልጥ እንድታድግ እንዴት ልንጠቀምበት

እንችላለን

እጅጋየሁ፡ ያለን የሀገር ፍቅር ይበልጥ በሥራ መዳበር አለበት።

አክሎግ፡ የኅብረተሰቡን ባህል፣ ሃይማኖት፣ እምነትና አመለካከት ማጥናትና በምርምር ማሳደግ

መስከረም፡ በጎሳ፣ በሃማኖት፣ በብሔር፣ በፖለቲካ የእርስ በርስ ግጭቶችን እንዳይፈጠሩ

በማስተማር

ኦኮክ፡ በተሰማራንበት የሥራ መስክ በታማኝነት በማገልገልና ሙሰኛ ባለመሆን።

መምህር፡ እጅግ በጣም ጥሩ!! በኢትዮጵያዊነት ርዕስ የጀመርነውን ውይይት ከማጠቃለላችን

በፊት የምትጨምሩት ሐሳብ ካለ?

ፍልይቲ፡ ከውጭ ሀገራት ጣልቃ ገብነት ሀገራችንን መከላከልና መጠበቅ።

ነስሩ፡ የውጭ ሀገራት ባህሎችና አስተሳሰቦች የሀገራችንን ባህልና አስተሳሰብ እንዳይበክሉ ወጣቶችን ማስተማር ኢትዮጵያዊነታችንን ለመጠበቅ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው።

መምህር፡ በጣም ጥሩ ተሳትፎ አድርጋችኋል። ኢትዮጵያዊነታችን ተጠብቆና ተከብሮ እንዲቀጥ

የሁላችንም ድርሻ የጎላ ነው።

## መልመጃ አንድ

ከዚህ በላይ የቀረበውን ውይይት መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በኢምቋ መልሱ።

1. በውይይቱ ውስጥ ከቀረቡት የሀገር ፍቅር መገለጫዎች ሦስቱን ዘርዝሩ።
2. የሀገር ፍቅር ወይም የኢትዮጵያዊነት ስሜት አለመኖር ምን-ምን ጉዳቶችን ያስከትላል?
3. ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት እንዳትያዝ ያደረጓት ምክንያቶች ምን-ምን ናቸው?
4. ከውይይቱ እንደተረዳችሁት ኢትዮጵያን ከሌሎች ሀገራት ለየት የሚያደርጋት ምንድን ነው?
5. ኢትዮጵያ ቋንቋዎቿ፣ ባህሏ፣ ድንበሯ፣ ወዘተ፣ ተከብሮና ተጠብቆ የኖረው በምን ምክንያት

ነው?

6. ለውይይቱ የራሳችሁን ርእስ ስጡት?
7. የሀገር ፍቅርና ኢትዮጵያዊነትን ተጠብቆና ተከብሮ እንዲቆይና ለትውልድ እንዲተላለፍ ምን መደረግ አለበት?

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### የኢምቁ አገባባዊ አገላለጽ

ከምንባቡ የተውጣጡ ቁልፍ ምልክቶች እንደ አገባባቸው ሲገለጹ፡፡

ምሳሌ አንድ አንድ ድምጽ

1. ተማሪዎቹ እሺ መምህር በማለት በአንድ ድምጽ መለሱ፡፡
2. በሀገራዊ ምርጫ ወቅት አንድ ሰው መስጠት የሚችለው አንድ ድምጽ ብቻ ነው፡፡

ምሳሌ ሁለት ማለት

1. “ኢትዮጵያዊነት ማለት ምን ማለት ነው?” በማለት መምህሩ ተማሪዎችን ጠየቁ፡፡
2. “እኔ ማለት የፈለኩት ተማሪዎች በጣም ጎበዞች ናቸው፡፡” ብሎ ንግግሩን አስተባበለ፡፡

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በላይ የቀረበውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በተለያየ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን የተለያየ ምልክቶች ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. ማስደፈር

ሴቶች ክብረ ንጽሕናቸውን ማስደፈር የለባቸውም፡፡

ሉዓላዊነታችንን አለማስደፈር የኢትዮጵያዊነታችን መገለጫ ነው፡፡

2. መገዛት

በቅኝ ግዛት መገዛት ቋንቋና ባህልን በመደባለቅ ማንነትን ያሳጣል፡፡

ለአምላካችሁ መገዛት ዕድሜአችሁን ያረዝመዋል፡፡